# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ለሥራ ተቋራጮች ለሚሰጠው ፈቃድና ቁጥጥር ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የአሰራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

መጋቢት 2009 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ማውጫ


ማውጫ ........................................ i

ማጠቃለያ (Executive Summery)........................................ I

ክፍል አንድ ........................................ 1

መግቢያ........................................ 1

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ራዕይ እና ተልዕኮ ........................................ 2

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ዓላማ ........................................ 3

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ስልጣንና ተግባር........................................ 3

የሚኒስቴር ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል ........................................ 4

የሚኒስቴር መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ ........................................ 5

የኦዲቱ ዓላማ........................................ 5

ለክዋኔ ኦዲቱ የተለየው የኦዲት አካባቢ ........................................ 6

የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎችና የመመዘኛ መስፈርቶች ........................................ 6

የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ........................................ 7

የሥራ ተቋራጮች እና የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች ምዝገባ፣ ድጋፋና ክትትል፣ ኢንስፔክሽን እና ግብረ - መልስ የሥራ ፍሰት መግለጫ (System Description)........................................ 7

የሥራ ተቋራጮች ምዝገባና እድሳት ሂደት የስራ ፍሰት ........................................ 7

የሥራ ተቋራጮች ክትትል እና ድጋፍ፣ ኢንስፔክሽንና ግብረ-መልስ ሂደት የስራ ፍሰት፣........ 8

የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች ምዝገባ ፣ እድሳት፣ ድጋፍ፣ ክትትልና ........................................ 9

ኢንስፔክሽን የስራ ፍሰት ........................................ 9

የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ክትትል፣ ድጋፍና ኢንስፔክሽን ........................................ 10

ክፍል ሁለት ........................................ 12

የኦዲት ግኝቶች ........................................ 12

2.1 ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለስራ ተቋራጮች የሚሰጠው የብቃት ማረጋገጫ፣ ምዝገባና ቁጥጥር እንዲሁም ከሚመለከታቸው የመንግስት መ/ቤቶች እና ባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር መኖሩን በተመለከተ የወጡ ደንቦችና መመሪያዎች ማስፈፀም የሚያስችል ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ የአሠራር ስርዓት መዘርጋቱን እና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፣ ..... 12

የሥራ ተቋራጮች ፈቃድ አሰጣጥን የሚመለከቱ አዋጆችን ለማስፈፀም የሚረዱ ደንቦችና መመሪያዎች ጸድቀው ተግባራዊ መደረጋቸውን በተመለከተ፣ ..... 12

በሥራ ተቋራጮች ዙሪያ የተሰሩ ጥናቶችን በተመለከተ፣.........Error! Bookmark not defined.

ለሀገር በቀል ሥራ ተቋራጮች የሚደረገውን ድጋፍ በተመለከተ፣ ..... 17

ሥራ ተቋራጮች በየፕሮጀክቶቻቸው የሚያሰማሯቸው ሠራተኞችን በተመለከተ፣ ..... 19

ለአገር ውስጥ ሥራ ተቋራጮች የሚሰጡ ሥልጠናዎችን በተመለከተ፣ ..... 20

ፈቃድ የወሰዱ ሥራ ተቋራጮች በየዓመቱ ማሳደሳቸውን መቆጣጠርና መከታተልን በተመለከተ፣ ..... 21

የመሳሪያዎች/ ተሽከርካሪዎች ዝርዝር መረጃዎች ወቅታዊ የሚደረጉበት ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ሥርዓትን በተመለከተ፣ ..... 24

ፈቃዳቸውን ለሌላ አካል አሳልፈው የሚሰጡ የስራ ተቋራጮችን በተመለከተ፣ ..... 26

የሥራ ተቋራጮች የአገልግሎት መስጫ የጊዜ ገደብና የተገልጋዮች ፍላጎት እርካታን በተመለከተ፣ ..... 26

ለመንግስትና ለህዝብ አገልግሎት በሚውሉ ግንባታዎች ላይ የሚደረግ የክዋኔ ኦዲትን በተመለከተ፣ ..... 29

የፌዴራልና የክልሎች የኮንስትራክሽን ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ ተመሳሳይ ስታንዳርድ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፣ ..... 29

2.1.2 ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው የመንግስት መ/ቤቶች እና ባለድርሻ አካላት ጋር የሥራ ተቋራጮችን ውጤታማ ለማድረግ እና ለመደገፍ በቅንጅት የሚሰሩበት አሰራር መዘርጋቱንና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፣ ..... 31

ከባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ የሚደረግ ቁጥጥርና ክትትልን በተመለከተ፣ ..... 31

በፌዴራል ደረጃ ብቻ የሚሰጡ አገልግሎቶችን በተመለከተ፣ ..... 32

ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን ግንኙነት በተመለከተ፣ ........ 32

2.2 የሥራ ተቋራጮችን የሚመለከቱ መረጃዎች አያያዝ እና አጠባበቅ እንዲሁም ቀልጣፋ የሆነ የመረጃ ልውውጥ ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፤ ........ 33

ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን የመረጃ ልውውጥ በተመለከተ፣ ........ 33

ስለ ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የሚተነተኑ መረጃዎች ስርጭትን በተመለከተ፣ ........ 34

ፈቃድ የወሰዱ ሥራ ተቋራጮችን የሚመለከቱ ማስረጃዎች በጥንቃቄ መያዛቸውን በተመለከተ፣ ........ 35

ክፍል ሶስት ........ 37

መደምደሚያ ........ 37

ክፍል አራት ........ 39

የማሻሻያ ሃሳቦች ........ 39

አባሪ 1፡ የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ድርጅታዊ መዋቅር ........ 43

አባሪ 2፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria) ........ 44

አባሪ 3፡ በኦዲቱ ወቅት በናሙና የታዩ ቢሮዎች፣ ሥራ ተቋራጮች እና ባለድርሻ አካላት እና ዝርዝር ........ 49

## ማጠቃለያ (Executive Summery)

የክዋኔ ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (Ethiopian Performance Audit Standards) እና ለመ/ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 982/2008 ዓ.ም በተሰጠው ስልጣን መሰረት ሲሆን ኦዲቱ ለሥራ ተቋራጮች ለሚሰጠው ፈቃድና ቁጥጥር ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የአሰራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው፡፡ ዝርዝር ኦዲቱ የሸፈነው የሶስት በጀት ዓመታትን ከ2006 - 2008 ዓ.ም እና የ2009 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የሥራ ክንውኖችን በማካተት ነው፡፡

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ለአገሪቱ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት መፋጠን ወሳኝ የሆኑ መሰረተ ልማቶችን የማስፋፋት ተልዕኮውን በብቃት መወጣት የሚችል፣ ከሌሎች የምርትና አገልግሎት ዘርፎች ጋር የጠበቀ ትስስር እንዲኖውና በአለም አቀፍ ደረጃ የመወዳደር አቅም እየገነባ በቀጣይነት እንዲያድግ ለማድረግ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን የሚመራ ራሱን የቻለ ተቋም እንዲኖር በመወሰኑ የአስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 ዓ.ም መሰረት የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ራሱን ችሎ እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡

በመሆኑም ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ሊፈጽማቸው ሲገባ ያልፈጸማቸው ዋና ዋና ግኝቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- የአስፈፃሚ አካላት መቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 691/2002 ለቀድሞው ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የተሰጠውን ስልጣን ተከትሎ የሥራ ተቋራጮች ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር ደንብ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ያልወጣ መሆኑ፡ ነገር ግን ማፈጸሚያ ደንቡ ሳያዘጋጅ ሚኒስቴር መ/ቤቱ መመሪያ ቁ. 19 (የባለሙያዎችና የሥራ ተቋራጮች ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ እና 22 (የአማካሪዎች ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ) አዘጋጅቶ እየተጠቀመበት መሆኑ፣
- በሁሉም ዓይነት የስራ ተቋራጭነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለመውሰድ የመጡ ስራ ተቋራጮች የሚያቀርቧቸው እና መሟላት ያለባቸውን መሳሪያዎችና ተሽከርካሪዎች በሰነድ መኖራቸውን የሚያረጋግጥ ቢሆንም በአካል መኖራቸውን በተመለከተ ግን ፈቃድ ሲሰጥም ሆነ ሲያሳድሱ የማያረጋግጥ መሆኑ፣ እንዲሁም ሥራ ተቋራጮች በሰነድ የሚያቀርቧቸው የሰው ኃይል (Minimimum man power

requirement) የስራ ውል ስምምነት ከፈፀሙ በኋላ ስራ ላይ መኖራቸው እና አለመኖራቸው የማይረጋገጥ መሆኑ፣

- የሥራ ተቋራጮች በየፕሮጀክቶቻቸው የሚያሰማሯቸው ሠራተኞች የብቃት ደረጃ ከሚወስዷቸው የግንባታ ኮንትራቶች እና ሰራተኞቹን ከሚያሠሯቸው ተግባር ጋር ተመጣጣኝ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፣
- በፌዴራል ደረጃ ፈቃድ የወሰዱ ሥራ ተቋራጮች በየዓመቱ ፈቃዳቸውን ማደሳቸውን የማይከታተልና የማይቆጣጠር በመሆኑ እስከ 2008 ዓ.ም ድረስ ከ11,912 ስራ ተቋራጮች ውስጥ 5,321 ስራ ተቋራጮች ፈቃድ ያላሳደሱ ሲሆን ህብረተሰቡ፣ የግል ድርጅቶች፣ የመንግስት ተቋማት እና የሚመለከታቸው ዋና ዋና ባለድርሻ አካላት እንዲያውቁት ያላደረገ መሆኑ፣
- የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች/ ተሽከርካሪዎች ዝርዝር መረጃ የባለቤትነት እና ሌሎች ተያያዥ ሁኔታዎች የሚያሳዩ መረጃዎች የሚመዘገብትና ወቅታዊ የሚደረግበት ዘመናዊ መረጃዎች አያያዝ ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ እንዲሁም የሥራ ተቋራጮች የሚያቀርቧቸው ሊብሬዎች እና የመኪና ሽያጭ ውል ወይም ዲክላሬሲዮን 3ኛ ወገን እና ተያዥ ሰነዶችን ሲያቀርቡ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ትክክለኛነቱን ፈቃድ ሲያወጡ ያቀረቡትን ተሽከርካሪ በእድሳት ወቅት ሲያመጡ አጠራጣሪና ሐሰተኛ ሆነው ሲገኙ የማያጣራ መሆኑ፣ በአንድ የኮንስትራክሽን ማሽነሪ/ ተሽከርካሪ በድጋሚ ሌሎች ፈቃድ እንዳያወጡ ለማጣራት የሚያስችለው የአሰራር ሥርዓት ያልዘረጋ መሆኑን፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከተሠጣቸው ደረጃ ውጭ የሚሰሩ የሥራ ተቋራጮች እንዳይኖሩ ለመከላከል የሚያስችል የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አለማድረጉ፣
- በፌዴራል ደረጃ ብቻ የሚሰጡ አገልግሎቶች ተጠቃሚዎች በቀላሉ/በያሉበት ቦታ ወይም በቅርበት አገልግሎቱን እንዲያገኙ ለማድረግ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት ያልዘረጋ መሆኑ፣

ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ ከላይ የተመለከቱት ግኝቶች መፍትሄ የማያገኙ ከሆነ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ለአገሪቱ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት ለማፋጠን እና ተልዕኮውን በብቃት መወጣት እንዳይችል እና የመልካም አስተዳደር ችግር እንዲጋለጥ ሊያደርገው

እንደሚችል በኦዲቱ ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም ችግሮችን ለመቅረፍ የሚያስችሉ የማሻሻያ ሃሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የምዝገባና የፈቃድ አሰጣጥ ሂደቱን በአግባቡ ለመምራት ስታንዳርዱን የጠበቀ እና ከወቅቱ ፍላጎት ጋር የተጣጣመ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችሉ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች አውጥቶ በማፀደቅ ተግባራዊ ማድረግ እንዲሁም አዋጆች፣ ደንብና መመሪያዎች ከመፅደቃቸው በፊትም ሆነ በኋላ የሚመለከታቸው አካላት ሃሳብ/አስተያየት እንዲሰጡበት ማድረግ አለበት፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሁሉም ዓይነት የስራ ተቋራጭነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለመውሰድ እና በየዓመቱ ፈቃዳቸውን ለማሳደስ የሚመጡ ሥራ ተቋራጮች በሰነድ የሚያቀርቧቸው መሳሪያዎች፣ ተሽከርካሪዎችና የሰው ኃይል በአካል መኖራቸውን የሚያረጋግጥበት የአሰራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ተቋራጮች በየፕሮጀክቶቻቸው የሚያሰማሯቸው ሠራተኞች የብቃት ደረጃ እና የግንባታ ኮንትራቶች ከሚያሠሯቸው ተግባር ጋር ተመጣጣኝ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችለውን ስልት በመንደፍ ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፈቃድ የወሰዱ ሥራ ተቋራጮች በየዓመቱ የእድሳት ጊዜያቸውን ጠብቀው እንዲያሳድሱ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግና በቁጥጥሩና ክትትሉ መሰረት ፈቃዳቸውን ያላሳደሱ ሥራ ተቋራጮችን ዝርዝር የተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች (ቴሌቪዥን፣ ሬዲዮ፣ ጋዜጣ፣ ዌብሳይት .... ወዘተ) በመጠቀም ህብረተሰቡ፣ የግል ድርጅቶች፣ የመንግስት ተቋማት እና የሚመለከታቸው አካላት እንዲያውቁት፣ (ህጋዊ ባልሆነ) በፎርጅድ እድሳት የሚንቀሳቀሱ ስራ ተቋራጮች ቁጥር እንዲቀንስ እና ህብረተሰቡ በሕገ-ወጥ ሰነድ በሚንቀሳቀሱ አካላት እንዳይታለል ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፈቃድ የወሰዱ ስራ ተቋራጮች የብቃት ማረጋገጫውን ለማግኘት ያስመዘገቧቸውን (የሰው ኃይል፣ መሳሪያዎችና ተሽከርካሪዎች) ለተባለለት ዓላማ/ሥራ እየዋሉ መሆናቸውን በየዓመቱ በእቅድ ይዞ በማረጋገጥ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድባቸው የሚያስችለውን ሁኔታ ሊያመቻች ይገባል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአንድ መሳሪያ ብዛት ያላቸው የሥራ ተቋራጮች ፈቃድ እንዳያወጡ ለማድረግ የመሳሪያዎች/ተሽከርካሪዎች ዝርዝር መረጃ የባለቤትነት እና ሌሎች ተያያዥ ሁኔታዎች የሚሳዩ መረጃዎችን በመመዝገብና ወቅታዊ በማድረግ ሕገ-ወጥ የተሽከርካሪ/መሳሪያዎች ማስረጃዎችን መከላከል አለበት፡፡

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ጥንታዊ የግንባታ ቅርሶች የአገሪቱ የኮንስትራክሽን ጥበብ ረጅም ዘመናትን ያስቆጠረ መሆኑን የሚያሳዩ ቋሚ ምስክሮች ናቸው፡፡ ከነዚህ ውስጥም ለአብነት የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት፣ የአክሱም ሃውልቶችና የሐረር ግንብ ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ ከዚህ የምንረዳው በዚያን ወቅት የሰለጠነ የግንባታ ባለሙያና ሥራዎችን ለመምራት የሚያስችል የግንባታ ሥራ አመራር እንደነበረ ነው፡፡በኋለኛው ዘመን ግን ሥልጣኔው በጦርነት ምክንያት እየጠፋና እየወደቀ ሲሄድ ጥበቡም የሚስፋፋበት ምቹ ሁኔታዎች ባለመኖራቸው የግንባታ ሥራዎች ለረጅም ጊዜያት በበቂ ደረጃ አልነበሩም፡፡ በዚህም ምክንያት ሥራው በአብዛኛው በውጪ ባለሙያዎች ድጋፍ ላይ እንዲወድቅ አድርጎት እንደነበረ ይታወሳል፡፡

2. ከመቶ ዓመታት ወዲህ ግን በመጠኑ እየተሻሻለ መጥቶ በአጼ ኃይሌ ሥላሴ ዘመነ መንግስት በተቋም ደረጃ የገጠር ፕሮጀክቶች ሥራና ሌሎችም በከተማ ውስጥ የግንባታ ኃይል መደራጀት የጀመረ ሲሆን በአገሪቱ ለህንጻ ኮንስትራክሽን የሚውሉ ሥራዎችን በማዕከላዊ ደረጃ ለመምራት ለመቆጣጠርና ለብሔራዊ ኢኮኖሚው አስተዋጽኦ እንዲያደርግ፣ የህንጻ ኮንስትራክሽን በብሔራዊና ዓለም አቀፍ ደረጃ ራሳቸውን ችለው እንዲሠሩ ማደራጀትና ማጠናከር እንዲቻልና፣ የህንጻ ኮንስትራክሽን እንዲስፋፋ በመንግሥታዊና ህዝባዊ ድርጅቶች፣ ራስ አገዝ፣ ፕሮግራሞች፣ የሠፊውን ህዝብ የጉልበትና ማቴሪያል አስተዋጽኦና ተሳትፎ ለማስተባበር እንዲያስችል የኢትዮጵያ ህንጻ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን (EBCA) በአዋጅ ቁጥር 191/1972 ዓ.ም ተጠሪነቱ ለቤቶች፣ ከተማ ልማት እና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ሆኖ ተቋቁሟል፡፡

3. በመቀጠልም የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 216/1974 ዓ.ም እንዲቋቋም ሲደረግ ቀደም ሲል የተቋቋመውን የኮንስትራክሽን ባለሥልጣን መ/ቤትን በመተካትና ከቤቶች፣ ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በመለየት ራሱን ችሎ የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በሚል ተቋቁሞ ነበር፡፡ በወቅቱ የተሰጡት ኃላፊነቶች የኮንስትራክሽን ፖሊሲና ስትራቴጂክ ፕላን ማዘጋጀት፣ የህንጻና የትራንስፖርት መሰረት አገልግሎቶች (መሠረተ ልማት) የኮንስትራክሽን ደንብ፣ ደረጃ፣ ማውጣት

የኮንስትራክሽን ሥራ የሚያካሂዱ ድርጅቶች ማቋቋም፣ የአማካሪነት አገልግሎት፣ የአማካሪነትና የኮንትራክተር ፈቃድ መስጠት፣ የባለሙያዎችን መመዝገብና ደረጃ ማውጣት፣ የቴክኖሎጂና የማቴሪያል ምርምር ያካሂዳል፣ የግብዓት ዓይነት ጥራትን መወሰን እንደ አስፈላጊነቱ ኮንስትራክሽንን በተመለከተ በከፊል ውክልና መስጠት የሚሉ ይገኙበታል፡፡

4. የሚኒስቴር መ/ቤቱም በተሠጠው ኃላፊነት መሠረት የተለያዩ የኮንስትራክሽንና የሬጉላቶሪውን ሥራ የሚሠሩ የህንጻና የትራንስፖርት ዲዛይን ባለሥልጣን (BATCoDA)፣ የህንጻ ዲዛይን ኢንተርፕራይዝ እና እንደ ጥቁር ዓባይ ኮንስትራክሽን የመሳሰሉ የተለያዩ የኮንስትራክሽን ድርጅቶችን በማቋቋም በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ዘርፍ የማማከር እና የግንባታ ሥራዎች ሙሉ በሙሉ በመንግሥት እንዲሠራ በማድረግ በወቅቱ እየበቀሉ የነበሩትን ኢትዮጵያዊ የሥራ ተቋራጮች በሙሉ እንዲወረሱ አድርጓል፡፡

5. ከደርግ መንግስት በኋላም የኮንስትራክሽን ዘርፉ ከከተማ ልማት ጋር በመሆን እስከ መስከረም 2008 ድረስ በጋራ ሲሰራ ቆይታል፡፡ ይሁን እንጂ የኢፌዲሪ መንግስት የሚከተለው ነጻ የኢኮኖሚ ፖሊሲ የግል ሴክተሩ መሪ ተዋናይ እንዲሆን በማድረጉና የግል አማካሪዎችና የሥራ ተቋራጮች እንዲቋቋሙ በመፍቀዱ ኢንዱስትሪው የተሻለ እንቅስቃሴ እንዲያሳይ ዕድል ተፈጥሯል፡፡ በመሆኑም ኢኮኖሚው በየዓመቱ በባለሁለት አኃዝ እድገት በማሳየቱና ለውጥ በመምጣቱ ፣ ከኢኮኖሚው እድገት ጋር ተያይዞም መዋቅራዊ ለውጥ በማስፈለጉ መንግሥት ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን የሚመራ ራሱን የቻለ ተቋም እንዲኖር በመወሰኑ የአስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 ዓ.ም መሰረት የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ተብሎ ራሱን ችሎ ተቋቁሟል፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ ራዕይ እና ተልዕኮ

**ራዕይ** (Vision)

6. በ2017 በክፍለ አህጉራዊና በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆነ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ተፈጥሮ ማየት፡፡

**ተልዕኮ** (Mission)

7. የዘርፉን ተገልጋዮችና ባለድርሻ አካላት በማስተባበርና በማቀናጀት ደረጃውን የጠበቀና ተወዳዳሪ የሆነ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ በመገንባት አገራዊ የልማት ራዕይን እውን ማድረግ፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ ዓላማ

8. የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ለአገሪቱ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት መፋጠን ወሳኝ የሆኑ መሰረተ ልማቶችን የማስፋፋት ተልዕኮውን በብቃት መወጣት የሚችል፣ ከሌሎች የምርትና አገልግሎት ዘርፎች ጋር የጠበቀ ትስስር ያለውና በአለም አቀፍ ደረጃ የመወዳደር አቅም እየገነባ በቀጣይነት እንዲያድግ ማድረግ ነው፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ ስልጣንና ተግባር

9. የአስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 ዓ.ም መሰረት ለኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ተሰጥቶቷል፡-

ሀ/ ለሌሎች አካላት በሕግ የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የኮንስትራክሽን ሥራዎችን ደረጃ ያወጣል፣ መከበራቸውን ይከታተላል፣

ለ/ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተወዳዳሪነት ብቃት ያለው የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ለመገንባት የሚያስችሉ የተመቻቹ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ያደርጋል፣

ሐ/ በፌዴራል መንግሥት በጀት ለሚሠሩ ሕንፃዎች ዲዛይኖችና የግንባታ ውሎች እንዲዘጋጁ በማድረግና የግንባታ ሥራዎችን በመቆጣጠር ረገድ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤

መ/ በኮንስትራክሽን ዘርፍ የሚሰማሩ መሐንዲሶችና አርክቴክቶችን ይመዘግባል፣ የሙያ ችሎታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ የሥራ ተቋራጮችንና የአማካሪዎችን ደረጃ ይወስናል፣ ከአንድ በላይ በሆኑ ክልሎች ውስጥ መሥራት ለሚችሉ የሥራ ተቋራጮችና አማካሪዎች የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

ሠ/ አገር በቀል የኮንስትራክሽን ድርጅቶችን ብቃትና ቀጣይነት ለማረጋገጥ የሚያስችል ስትራቴጂ ይቀይሳል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

ረ/ በአገር ውስጥ የሚመረቱ የኮንስትራክሽን ዕቃዎችን ዓይነትና ጥራት ለማሻሻል የሚረዳ ምርምር ያካሂዳል፤

ሰ/ የህንጻ ኮድና ስታንዳርዶች በከተሞች ተፈጻሚ እንዲሆኑ ተገቢው አደረጃጀት፣ አሠራርና የሰው ኃይል አቅም እንዲፈጠር ያደርጋል፣ አፈፃፀሙን ይደግፋል፣ ይከታተላል፤

የሚል ሲሆን በተጨማሪም፡- በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች ድንጋጌዎች ኮንስትራክሽንን የሚመለከት ለከተማ ልማት፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ተሰጥተው የነበሩ ስልጣንና ተግባሮች በዚህ አዋጅ ለኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ተሰጥተዋል፡፡

## የሚኒስቴር ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል

### ድርጅታዊ መዋቅር

10. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመራው የተቋሙ የበላይ አመራር በሆኑ በአንድ ሚኒስትር እና በሁለት ሚኒስትር ዴኤታዎች ሲሆን ተጠሪነቱም ለጠቅላይ ሚኒስትሩ እና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ነው፡፡ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በሁለት በሚኒስትር ዴኤታዎች ማለትም በአቅም ግንባታና የቴክኖሎጂ ሽግግር ዘርፍ እና በሬጉላቶሪ ዘርፍ የተዋቀረ ሲሆን በስራቸው 28 ዳይሬክትሬክቶች አሉ፡፡ እንዲሁም ለሚኒስትር መ/ቤቱ ተጠሪ የሆነ የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት ይገኛል፡፡ ድርጅታዊ መዋቅሩ በአባሪ 1 ተያይዟል፡፡

### የሰው ኃይል

11. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በታህሳስ 2009 ዓ.ም 61 (31%) ሴት ሠራተኞች 135 (68%) ወንድ ሠራተኞች በድምሩ 196 ቋሚ ሠራተኞች ያሉት ሲሆን፣ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ያለው የቋሚ ሠራተኞች የሰው ኃይል በሙያ ሲተነተን ሁለተኛ ዲግሪ 37 (18%)፣ የመጀመሪያ ዲግሪ 87 (44%)፣ ዲፕሎማ 36 (18%) ሠርተፊኬትና ከዛ በታች ያሉ 36 (18%) ነው፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ

12. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በመቋቋሚያ አዋጅ 916/2008 የተሰጠውን ተግባር ለማስፈፀም ይረዳው ዘንድ ከመንግስት በጀት የሚመደብለት እና ከሚሰጡ አገልግሎቶችና ከተለያዩ ምንጮች ገቢ የሚያገኝ እና ፈሰስ የሚደረግ ሲሆን ቢሮው እስከ 2007 ዓ.ም በቀድሞው በከተማ ልማት ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ሥር በቢሮ ደረጃ ስለነበረ እንደ ቢሮ የተያዘለት በጀትና አጠቃቀም፣ ከአገልግሎቶች ሊሰበሰብ ያቀደው እና የሰበሰው የተጠቀሰ ሲሆን ከ2008-2009 ሩብ ዓመት ድረስ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የተመደበለት በጀትና ያወጣው ወጪ እንዲሁም ከሚሠጣቸው አገልግሎቶችና ከተለያዩ ምንጮች ያገኘው ገቢ በሚከተለው ሰንጠረዥ ተመልክቷል፡፡

| በጀት ዓመት | ከመደበኛ በጀት | | | ሚ/ር መ/ቤቱ ከሚሰጠው አገልግሎትና ከተለያዩ ምንጮች | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | የተፈቀደ | ስራ ላይ የዋለ | ሥራ ላይ የዋለው በ% | ለመሰብሰብ የታቀደ | የተሰበሰበ | የተሰበሰበው በመቶኛ |
| 2007 | 16,823,000 | 14,895,554 | 8.54% | 11,216,550 | 21,264,103 | 189.58% |
| 2008 | 46,147,822 | 31,722,310 | 68.32% | 24,395,000 | 25,017,070 | 102.55% |
| 2009 1ኛሩብ ዓመት) | 90,274,253 | 12,013,313.55 | 3.30% | 25,000,000 | 5,400,000 | 21.6% |

## የኦዲቱ ዓላማ

13. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ በኮንስትራክሽን ዘርፍ የተሰማሩ ተቋራጮች የሚሰጣቸው ፈቃድ አሰጣጥ ቀልጣፋ መሆኑን ሚኒስቴር መ/ቤቱም ቁጥጥር ማድረጉን እና ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መስራቱን እንዲሁም በሚኒስቴር መ/ቤቱ እና ፈቃድ በወሰዱ ሥራ ተቋራጮች መካከል ቀልጣፋ የሆነ የመረጃ ልውውጥ ስርዓት መዘርጋቱን እና ተግባራዊ መደረጉን ለማረጋገጥ ሲሆን፤ በዚህ ዙሪያ የሚታዩ ችግሮችን በመለየትና ችግሮችን ለማቃለል ብሎም ለማስወገድ የሚረዱ የማሻሻያ ሃሳቦችን ለማቅረብ ነው፡፡

## ለክዋኔ ኦዲቱ የተለየው የኦዲት አካባቢ

14. "ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለሥራ ተቋራጮች ለሚሰጠው ፈቃድና ቁጥጥር ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የአሰራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን መገምገም" የሚል ነው፡፡

## የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎችና የመመዘኛ መስፈርቶች

### የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች

15. ለተመረጠው የኦዲት አካባቢ (Audit Area) ሁለት ዋና እና ሁለት ንዑስ የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) ተለይተዋል፡፡ እነርሱም፡-

1. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለስራ ተቋራጮች የሚሰጠው የብቃት ማረጋገጫ፣ ምዝገባና ቁጥጥር እንዲሁም ከሚመለከታቸው የመንግስት መ/ቤቶች እና ባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር መኖሩን በተመለከተ የወጡ ደንቦችና መመሪያዎች ማስፈፀም የሚያስችል ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ የአሠራር ስርዓት መዘርጋቱን እና ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፣

    1.1 ሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ተቋራጮችን ብቃት በማረጋገጥ የሚመዘግብበት እና በየበጀት ዓመቱ ቁጥጥር የሚያደርግበት ሥርዓት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፣

    1.2 ሚኒስቴር መ/ቤቱ፣ ከሚመለከታቸው የመንግስት መ/ቤቶች እና ባለድርሻ አካላት ጋር የሥራ ተቋራጮችን ውጤታማ ለማድረግ እና ለመደገፍ በቅንጅት የሚሰሩበት አሰራር መዘርጋቱንና ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፣

2. የሥራ ተቋራጮችን የሚመለከቱ መረጃዎች አያያዝ እና አጠባበቅ እንዲሁም ቀልጣፋ የሆነ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፤ የሚሉ ናቸው፡፡

### የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶች

16. ከላይ የተለዩትን ሁለት ዋና እና ሁለት ንዑስ የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች ለመመዘን የሚረዱ 28 የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria)

ተዘጋጅተዋል፡፡ የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶችን ለማዘጋጀት መሰረት የሆኑት የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር መቋቋሚያ አዋጅ፣ ከ2003-07 እና ከ2008-2012 ዓ.ም ድረስ ያሉ ስትራቴጂክ እቅዶች፣ የኮንትራክተሮች ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያዎች፣ የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲ፣ ከ2006-2008 ዓ.ም ድረስ ያሉ የእቅድ ሪፖርቶች ፣የቢፒአር ሰነድ እና መልካም ተሞክሮዎች ናቸው፡፡ የተዘጋጁትን መመዘኛ መስፈርቶች ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ተልከው አስተያየት እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡ መመዘኛ መስፈርቶቹ በአባሪ 2 ተያይዘዋል፡፡

## የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

17. ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ ክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (Ethiopian Performance Audit Standards) እና ለመስሪያ ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ነው፡፡ ኦዲቱ የሸፈነው ከ2006 እስከ 2009 የመጀመሪያው ሩብ በጀት ዓመት ድረስ ያሉ የሥራ ክንውኖችን ነው፡፡

18. ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ሲሆን በተጨማሪም ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ጋር በቅርበት በሚሰሩ በናሙና ከተመረጡት ሁለት የኮንስትራክሽን ቢሮዎች (አዲስ አበባ እና ኦሮሚያ) ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ፈቃድ አውጥተው በሁሉም ክልሎች የሚሰሩ የዘጠና አንድ ሥራ ተቋራጮቸች ፋይሎችን በመከለስ፣ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ፈቃድ አውጥተው በኦሮሚያ ክልል በሚሰሩ ሶስት እና በአዲስ አበባ መስተዳድር በሚሰሩ ሰባት ስራ ተቋራጮች በመገኘት ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብና ማስረጃዎችን በመከለስ ነው፡፡በኦዲቱ ወቅት የታዩ ቢሮዎችና ስራ ተቋራጮች ዝርዝር በአባሪ 3 ተያይዟል፡፡

# የሥራ ተቋራጮች እና የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች ምዝገባ፣ ድጋፋና ክትትል፣ ኢንስፔክሽን እና ግብረ - መልስ የሥራ ፍሰት መግለጫ (System Description)

## የሥራ ተቋራጮች ምዝገባና እድሳት ሂደት የስራ ፍሰት

### ሀ. የሥራ ተቋራጮች አዲስ ምዝገባን በተመለከተ

19. የሥራ ተቋራጮች አዲስ ምዝገባ ጥያቄ እና መረጃ መቀበል፣ ለአዲስ ምዝገባ የሚቀርቡትን ማስረጃዎች ትክክለኛነት ማረጋገጥ፣ ለምዝገባ የሚቀርቡ ማስረጃዎች

በመስፈርቶቹ መሰረት መሟላቱን መገምገምና ማጣራት፣ የቀረበውን ሰነድ ዋናውና ኮፒ በማገናዘብ እና ፋይል መክፈት፣ የአገልግሎት ክፍያ ማስከፈል፣ ሰርተፊኬት ማዘጋጀት፣ ማፅደቅ (ፊርማና ቲተር) እና አስፈርሞ መስጠት፣ የተመዘገበ መሆኑን በኮምፒዩተር (ዳታ ቤዝ) አስገብቶ ፋይሉን ወደ መዝገብ ቤት መላክ እና ሪፖርት ማዘጋጀት፡፡

ለ. <u>የሥራ ተቋራጮች እድሳት ምዝገባን በተመለከተ፡-</u>

20. የሥራ ተቋራጮች እድሳት ምዝገባ ጥያቄ እና መረጃ መቀበል፣ ለእድሳት ምዝገባ የሚቀርቡትን ማስረጃዎች ትክክለኛነት ማረጋገጥ፣ ለምዝገባ የሚቀርቡ ማስረጃዎች በመስፈርቶቹ መሰረት መሟላቱን መገምገምና ማጣራት፣ ዋናውን ሰርተፊኬት መቀበል እና ፋይሉን ማውጣት፣ የአገልግሎት ክፍያ ማስከፈል፣ እድሳት ማድረግ፣ ማጽደቅ (ፊርማና ቲተር በማድረግ) እና አስፈርሞ መስጠት፣ የታደሰ መሆኑን በኮምፒዩተር (ዳታ ቤዝ) አስገብቶ ፋይሉን ወደ መዝገብ ቤት መላክ እና ሪፖርት ማዘጋጀት፡፡

## የሥራ ተቋራጮች ክትትል እና ድጋፍ፣ ኢንስፔክሽንና ግብረ-መልስ ሂደት የስራ ፍሰት፣

ሀ. <u>ክትትል እና ድጋፍ በተመለከተ፡-</u>

21. ፈቃድ የወሰዱ ስራ ተቋራጮችን መከታተል የሚያስችል ቼክ ሊስት እና የድርጊት መርሃ-ግብር ማዘጋጀት፣ ለክትትል የሚያስፈልጉ መረጃዎችን መለየት፣ ለክትትል እና ድጋፍ አስፈላጊ የሆኑ የክልል ኮንስትራክሽን ዘርፍ ተቋማት እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር (ባንክ፣ መንገድ ትራንስፖርት፣ የሙያ ማህበራት እና ኢንሹራንስ) የመረጃ ልውውጥ ማድረግ፣ ተቋራጮች የሚያቀርቧቸው የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች፣ ባለሙያዎች እና የተሽከርካሪ ማስረጃዎች የተሰጣቸውን የብቃት ማረጋገጫ የሚያሟሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣ በአንድ ተሽከርካሪ ተደጋጋሚ ምዝገባዎች እንዳይደረግ መከታተል፣ የእድሳት ጊዜ ሳያልፍባቸው እድሳት እንዲያደርጉ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣ ፈቃድ ያላደሱ ተቋራጮች ጨረታ ላይ እንዳይሳተፉ ለህብረተሰቡ፣ ለግል ገንቢዎች እና ለመንግስት ተቋማት ከዌብ ሳይት ላይ ያደሱ ስራ ተቋራጮች እንዲያጣሩ ግንዛቤ መፍጠር፣ የሚዘጋጁ ዓመታዊ ሪፖርቶችን፣ በምዝገባ ወቅት የቀረቡ ሰነዶችን እና ሌሎች መረጃዎች መሰረት በማድረግ ያቀረቧቸው የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች፣ ተሽከርካሪ እና ባለሙያ በስራ

ላይ መሆናቸውን መከታተል፣ ከሙያ ማህበራት ጋር ግንኙነት በማጠናከር ስራ ተቋራጮች በተሰጣቸው የብቃት ማረጋገጫ እየሰሩ መሆኑን መከታተል፣ ዓመታዊ የስራ አፈጻጸም ሪፖርት በወቅቱ ማድረጋቸውን ማረጋገጥ እና የሪፖርቱን ይዘት መመርመር፣ በወቅቱ ሪፖርት ያላደረጉት እንዲልኩ ክትትል እና ድጋፍ ማድረግ እና በድጋፍ እና ክትትል ወቅት የተገኙ መረጃዎችን ለኢንስፔክሽን እና ለሪፖርት በሚያመች መልኩ ማደራጀት ነው፡፡

ለ. **ኢንስፔክሽን በተመለከተ፡-**

22. ለኢንስፔክሽን የሚያገለግል ቼክሊስትና የድርጊት መርሃ ግብር ማዘጋጀት፣ መረጃዎችን መተንተንና የተገኙ ችግሮች መለየት፣ ኢንስፔክሽን ማካሄድ፣ በኢንስፔክሽን ወቅት የተገኙ ችግሮች ላይ በየደረጃው ውይይት ማድረግ፣ በተለዩ ችግሮች ላይ የመፍትሄ አቅጣጫ ማስቀመጥ እና እንደ ችግሮቹ ክብደት እየለዩ እርምጃ መውሰድ ናቸው፡፡

ሐ. **ግብረ-መልስ በተመለከተ፡-**

23. በክትትል፣ በድጋፍና ኢንስፔክሽን ስራዎች ላይ በታዩ ጠንካራና ደካማጎኖች የቃል እና የጽሁፍ ግብረ-መልስ መስጠት እና በተሰጠው ግብረ-መልስ መሰረት ሥራዎች መሰራታቸውን መከታተል ነው፡፡

## የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች ምዝገባ ፣ እድሳት፣ ድጋፍ፣ ክትትልና ኢንስፔክሽን የስራ ፍሰት

ሀ. **የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች አዲስ የቴክኒክ ምርመራ ብቃት ማረጋገጫ በተመለከተ፡-**

24. የኮንስትራክሽን መሣሪያ አዲስ ምዝገባ ጥያቄ፣ መሳሪያውን ለማስመዝገብ የሚያስፈልገውን ፍቃድ እና ሌሎች መረጃ መቀበል፣ የኮንስትራክሽን መሣሪያ ለአዲስ ምዝገባ የሚቀርቡትን ማስረጃዎች ትክክለኛነት ማረጋገጥ፣ የቀረበውን ሰነድ ዋናውና ኮፒ ማገናዘብ እና ፋይል መክፈት፣ የቴክኒክ ምርመራ ክፍያ ማስከፈል፣ የቴክኒክ ብቃት ምርመራ ማድረግ እና በተዘጋጀው ፎርም ላይ በምርመራ የተገኘውን የመሳሪያ መረጃ መሙላት፣ የመሳሪያው ብቃት ሲረጋገጥ የአገልግሎት ክፍያ ማስከፈል፣ መረጃውን በሊብሬ ላይ መሙላት እና አጽድቆ መስጠት፣ ለሠሌዳ ህትመት የሚያስፈልግ መረጃ ማዘጋጀት እና ለሚመለከተው ተቋም መላክ፣ የሰሌዳ

ህትመት መከታተል እና ህትመቱ እንደተጠናቀቀ አስፈርሞ መስጠት እና የቴክኒክ ብቃት ምርመራውን፣ የደብተር ቁጥር እና የሰሌዳ ቁጥር በኮምፒውተር (ዳታ ቤዝ) አስገብቶ ፋይሉን ወደ መዝገብ ቤት መላክ እና ሪፖርት ማዘጋጀት ነው፡፡

### ለ. የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች የቴክኒክ ምርመራ ብቃት እድሳት ማረጋገጫ በተመለከተ፡-

25. የኮንስትራክሽን መሣሪያ እድሳት ምዝገባ ጥያቄ እና መረጃ መቀበል፣ ለእድሳት ምዝገባ የሚቀርቡትን ማስረጃዎች ትክክለኛነት ማረጋገጥ፣ ለእድሳት ምዝገባ የሚቀርቡ ማስረጃዎች በመስፈርቶቹ መሰረት መሟላቱን መገምገምና ማጣራት፣ዋናውን ደብተር መቀበል፣ ፋይሉን ማውጣት እና የአገልግሎት ክፍያ ማስከፈል፣ የቴክኒክ ብቃት ምርመራ ማድረግ እና መረጃውን በፎርሙ ላይ መሙላት የመሳሪያው ብቃት ሲረጋገጥ የአገልግሎት ክፍያ ማስከፈል፣ በደብተር ላይ እድሳት ማድረግ፣ ቦሎ መስጠት፣ማጽደቅ (ፊርማና ቲተር) እና አስፈርሞ መስጠት፣ የታደሰ መሆኑን በኮምፒዩተር (ዳታ ቤዝ) አስገብቶ ፋይሉን ወደ መዝገብ ቤት መላክ እና ሪፖርት ማዘጋጀት፡፡

## የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ክትትል፣ ድጋፍና ኢንስፔክሽን

### ሀ. የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ክትትልና ድጋፍ በተመለከተ፡-

26. ፈቃድ የወሰዱ ስራ ተቋራጮችን መከታተል የሚያስችል ቼክ ሊስት እና የድርጊት መርሃ-ግብር ማዘጋጀት፣ ለክትትል የሚያስፈልጉ መረጃዎችን መለየት፣ ለክትትል እና ድጋፍ አስፈላጊ ከሆኑ የክልል ከ/ቤ/ኮንስትራክሽን ሚኒስትር ዘርፍ ተቋማት እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር (ባንክ፣ መንገድ ትራንስፖርት፣ የሙያ ማህበራት እና ኢንሹራንስ) የመረጃ ልውውጥ ማድረግ፣ ተቋራጮች የሚያቀርቧቸው የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች፣ ባለሙያዎች እና የተሽከርካሪ ማስረጃዎች የተሰጣቸውን የብቃት ማረጋገጫ የሚያሟሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣ በአንድ ተሽከርካሪ ተደጋጋሚ ምዝገባዎች እንዳይደረግ መከታተል፣ የእድሳት ጊዜ ሳያልፍባቸው እድሳት እንዲያደርጉ ድጋፍ እና ክትትል ማድረግ፣ ፈቃድ ያላደሱ ተቋረጮች ጨረታ ላይ እንዳይሳተፉ ለህብረተሰቡ፣ ለግል ገንቢዎች እና ለመንግስት ተቋማት ከዌብ ሳይት ላይ ያደሱ ስራ ተቋራጮች እንዲያጣሩ ግንዛቤ መፍጠር፣ ዓመታዊ ሪፖርት፣ በምዝገባ ወቅት የቀረቡ ሰነዶችን እና ሌሎች መረጃዎች መሰረት በማድረግ

ያቀረቧቸውን የኮንስትራክሽን መሳሪያዎችን፣ ተሽከርካሪ እና ባለሙያ በስራ ላይ መሆናቸውን መከታተል፣ ዓመታዊ የስራ አፈጻጸም ሪፖርት በወቅቱ ማድረጋቸውን ማረጋገጥ እና የሪፖርቱን ይዘት መመርመር፣ በወቅቱ ሪፖርት ያላደረጉት እንዲልኩ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣ በድጋፍ እና ክትትል ወቅት የተገኙ መረጃዎችን ለኢንስፔክሽን እና ለሪፖርት በሚያመች መልኩ ማደራጀት የሚሉ ናቸው፡፡

ለ. <u>**የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ኢንስፔክሽን በተመለከተ፡-**</u>

27. ለኢንስፔክሽን የሚያገለግል ቼክሊስትና የድርጊት መርሃ ግብር ማዘጋጀት፣ መረጃዎችን መተንተንና የተገኙ ችግሮችን መለየት፣ ኢንስፔክሽን ማካሄድ፣ በኢንስፔክሽን ወቅት የተገኙ ችግሮች ላይ በየደረጃው ውይይት ማድረግ ፣ በተለያዩ ችግሮች ላይ የመፍትሄ አቅጣጫ ማስቀመጥ እና እንደ ችግሮቹ ክብደት እርምጃ መውሰድ ነው፡፡

ሐ. <u>**የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ግብረ- መልስ በተመለከተ፡-**</u>

28. በክትትል፣ ድጋፍና ኢንስፔክሽን ስራዎች ላይ በታዩ ጠንካራና ደካማ ጎኖች የቃል እና የጽሁፍ ግብረ-መልስ መስጠት እና በተሰጠው ግብረ-መልስ መሰረት ስራዎች መሰራታቸውን መከታተል ነው፡፡

## ክፍል ሁለት

## የኦዲት ግኝቶች

**2.1 ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለስራ ተቋራጮች የሚሰጠው የብቃት ማረጋገጫ፣ ምዝገባና ቁጥጥር እንዲሁም ከሚመለከታቸው የመንግስት መ/ቤቶች እና ባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር መኖሩን በተመለከተ የወጡ ደንቦችና መመሪያዎች ማስፈፀም የሚያስችል ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ የአሠራር ስርዓት መዘርጋቱን እና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፣**

**2.1.1. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ተቋራጮችን ብቃት በማረጋገጥ የሚመዘግብበት እና በየበጀት ዓመቱ ቁጥጥር የሚያደርግበት ስርዓት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ ስለመሆኑ፣**

**የሥራ ተቋራጮች ፈቃድ አሰጣጥን የሚመለከቱ አዋጆችን ለማስፈፀም የሚረዱ ደንቦችና መመሪያዎች ጸድቀው ተግባራዊ መደረጋቸውን በተመለከተ፣**

29. በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ዘርፍ ለሚሰማሩ የሥራ ተቋራጮች ፈቃድ አሰጣጥን የሚመለከቱ አዋጆችን ለማስፈፀም የሚረዱ ደንቦችና መመሪያዎች ተዘጋጅተው በሚመለከተው አካል ጸድቀው ተግባራዊ ሊደረጉ ይገባል፡፡

30. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአስፈፃሚ አካላት መቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 691/2002 ለቀድሞው ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር እና በአዋጅ ቁጥር 916/2008 አንቀጽ 27/መ ለኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የተሰጠውን ስልጣን ተከትሎ የሥራ ተቋራጮች ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር ደንብ ኦዲቱ እስከ ተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ አልወጣም፡፡ ነገር ግን ማስፈጸሚያ ደንቡን ሳያዘጋጅ ሚኒስቴር መ/ቤቱ መመሪያ ቁ.19 (የባለሙያዎችና የሥራ ተቋራጮች ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ እና 22 (የአማካሪዎች ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ) ያዘጋጀ ሲሆን እስከ 2008 ዓ.ም መመሪያዎቹ ከመፅደቃቸው በፊት የተለያዩ ባለድርሻ

አካላትን በማሳተፍ ያላቸውን ሃሳብ/አስተያየት እንዲሰጡ ያላደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

31. በተጨማሪም የቀድሞው የከተማ ልማት ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር

- የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ምዝገባና ቁጥጥር ደንብ አዘጋጅቶ በሚመለከተው አካል ሳያጸድቅ ከ1993 ዓ.ም ጀምሮ መመሪያ በማዘጋጀት እየተጠቀመበት ሲሆን የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ራሱን ችሎ በአዋጅ ከተቋቋመ በኋላ በህዳር ወር 2009 ዓ.ም ረቂቅ ደንብ ተዘጋጅቶ ለባለድርሻ አካላት ለውይይት ያቀረበ ቢሆንም ያልፀደቀ መሆኑ ታውቋል፡፡
- በ2006 ዓ.ም የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ የምዝገባ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ረቂቅ ዝግጅት ሥራ ተጠናቆ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲጸድቅ እና ወደ አፈጻጸም እንዲገባ ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ቢታቀድም እስከ 2008 ዓ.ም ያላተከናወነና በ2009 ዓ.ም እቅድ ላይም ያላካተተ መሆኑ፣
- የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ የምዝገባ አዋጁን ተከትሎ የሚወጣውን የባለሙያዎች፣ የስራ ተቋራጮች፣ አማካሪዎች እና የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ደንብ ማዘጋጀት እና ጸድቆ በስራ ላይ እንዲውል በመከታተል ድጋፍ ለማድረግ ቢታቀድም እስከ 2008 ዓ.ም ያልተከናወነ ሲሆን በ2009 ዓ.ም እቅድ ላይ ያልተካተተ መሆኑ፣
- የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የምዝገባ ደንቡን ተከትሎ የሚወጣውን፣ የባለሙያዎች፣ ስራ ተቋራጮች፣ አማካሪዎች እና የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች መመሪያ በአማካሪ እንዲሰራ የስራ ዝርዝር ማዘጋጀት እና ስራውን መከታተል በ2007 ዓ.ም አቅዶ ያላከናወነ መሆኑ፣ በ2008 እና በ2009 በጀት ዓመታት እቅድ ላይም ያልተካተተ መሆኑ፣
- የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች የኪራይ አገልግሎት ረቂቅ መመሪያ ተዘጋጅቶ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ አመራር አቅርቦ እንዲጸድቅ ለማድረግ በ2007 እና 2008 ዓ.ም በዕቅድ ተይዞ ያልተከናወነ ሲሆን በ2009 ዓ.ም እቅድ ውስጥም ያልተካተተ መሆኑ፣ ፡
- በ2008 ዓ.ም የኮንስትራክሽን አዋጁን ለማስፈፀም እና የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን የአሰራር ሥርዓት ለማጠናከር የሚያስችሉ 3 የህግ ማዕቀፎችን (ደንብና መመሪያዎች) ለማዘጋጀት ታቅዶ ያልተከናወነ ሲሆን

በ2009 እቅድ ላይ 8 የሕግ ማዕቀፎችን ለማዘጋጀት በእቅድ የተያዘ ቢሆንም እስከ አንደኛው ሩብ ዓመት ድረስ በህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ላይ የደሰሳ ጥናት በማድረግ ሰነዶችን የመለየት ስራ የተሰራ ቢሆንም የሕግ ማዕቀፎቹ ግን ያልተሰሩ መሆናቸው፣

በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

32. ስለ ሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የሥራ ተቋራጮች ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር አዋጅን መሰረት በማድረግ ደንብ ሳይዘጋጅ መመሪያ ቁ. 19 እና 22 መዘጋጀቱን ያመኑ ሲሆን በመመሪያዎች ላይ ያሉ ችግሮች መመሪያው ከመጽደቁ/ከመውጣቱ በፊትም ሆነ በኋላ የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ ያላቸውን አስተያየት/ ሃሳብ እንዲሰጡ የማድረግ ስራ መሰራቱን ገልፀውዋል፡፡ በእቅድ ተይዘው አልተከናወኑም ስለተባሉ ነገሮች ማለትም የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ምዝገባና ቁጥጥር ደንብ አዘጋጅቶ በሚመለከተው አካል እንዲፀድቅ ሳያደርግ መመሪያ በማዘጋጀት እየተጠቀመበት መሆኑን በተመለከተ ትክክል መሆኑን፣ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የምዝገባ አዋጁን ተከትሎ የሚወጣውን ደንብና መመሪያዎች ማዘጋጀትና አፀድቆ ስራ ላይ ማዋልን በተመለከተ የምዝገባና ሌሎች ጉዳዮችን በማካተት በአጠቃላይ የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ተግባርና ኃላፊነት ማሻሻያ አዋጅ እየተዘጋጀ በመሆኑ፣ የምዝገባ ስራዎችን የሚመለከት ኤጀንሲ ለማቋቋም የሚያስችል ደንብ ተዘጋጅቶ የነበረና ያልፀደቀ በመሆኑ ስራዎች ሊሰሩ አለመቻላቸውን፤ በተላከላቸው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (Fact Sheet) ላይ በሰጡት አስተያየት የገለፁ ሲሆን በተጨማሪም መመሪያዎች ከመፅደቃቸው በፊት ባለድርሻ አካላትን ያሳተፉ መሆናቸውን እና ማስረጃውን ማቅረብ እንደሚችሉ በመውጫ ስብሰባ ወቅት ገልፀዋል፡፡

33. ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በመመሪያዎቹ ዙሪያ ያሉ ችግሮች ከመፅደቃቸው በፊት ባለድርሻ አካላት የተሳተፉ መሆናቸውን የሚያሳዩ ማስረጃዎች ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ባለመቅረቡ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

34. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ተቋራጮችን የሚመለከቱ ደንብ፣ መመሪያና ሕጎች በእቅዱ መሰረት እንዲወጡ አለማድረጉ፣ ሥራዎች በግልጽነት እና ተጠያቂነት ባለበት መንገድ እንዳይከናወን እና የሚኒስቴር መ/ቤቱ እና ተገልጋዮች መብትና

ግዴታ እንዳይታወቅ በማድረግ ተገልጋዮችን ለአስፈላጊ እንግልት እንዲዳረጉ በማድረግ የመልካም አስተዳደር ችግር እንዲኖር ሊያደርግ ይችላል፡፡

## የሥራ ተቋራጮች የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድና እድሳትን በተመለከተ፣

35. ለሁሉም አይነት ሥራ ተቋራጮች (ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ፣ የህንፃ ሥራ ተቋራጭ፣ የመንገድ ሥራ ተቋራጭ እና ልዩ ሥራ ተቋራጭ) የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሲሰጥ በየደረጃው የተቀመጠውን መስፈርት (የመሳሪያ፣ የተሽከርካሪና የሰው ኃይል) ያሟሉ መሆኑ የሚያረጋግጥበት፣ በእድሳት ወቅትም በሰነድና በአካል መኖራቸው የሚረጋግጥበት የአሠራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

36. ይህን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሁሉም ዓይነት የስራ ተቋራጭነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለመውሰድ የመጡ ስራ ተቋራጮች፡-

- የሚያቀርቧቸው እና መሟላት ያለባቸውን መሳሪያዎችና ተሽከርካሪዎች በሰነድ መኖራቸውን የሚያረጋግጥ ቢሆንም በአካል መኖራቸውን በተመለከተ ግን ፈቃድ ሲሰጥም ሆነ ሲያሳድሱ የማያረጋግጥ መሆኑ፣
- ሥራ ተቋራጮች በሰነድ ያቀረቡት የሰው ኃይል (Minimimum man power requirement) የስራ ውል ስምምነት ከፈፀሙ በኋላ በሰነድ ላይ ያቀረቡት የሰው ኃይል ስራ ላይ ስለመኖራቸው የማይረጋገጥ መሆኑ፣
- ሥራ ተቋራጮች ፍቃድ ለመውሰድ በ Minimimum requirement ያስመዘገቧቸውን መሳሪያዎች ለሚኒስቴር መ/ቤቱን ሳያሳውቁ እያከራዩ መሆኑ እና ሚኒስቴር መ/ቤቱም ይህን ለመከታተል የሚያስችል ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ በማድረግ እርምጃ ያልወሰደ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

37. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ማህደራቸው ከታየ የ91 ሥራ ተቋራጮች ማህደር ውስጥ

- 18ቱ በእድሳት ወቅት የሚጠበቅባቸውን መሳሪያና ተሽከርካሪ በከፊል ያላሟሉ መሆኑ፣ 4ቱ በእድሳት ወቅት የሚጠበቅባቸውን የሰው ሃይል በከፊል ያላሟሉ መሆኑ፣

- በእድሳት ወቅት የሚደረግን የመሳሪያዎችና የተሸከርካዎች የቴክኒክ ምርመራን በተመለከተ ከ 91ዱ ሥራ ተቋራጮች ውስጥ 21ዱ ከ2006-2008 ዓ.ም ድረስ የቴክኒክ ምርመራ ያላደረጉ፣ 22ቱ ለተወሰኑ ተሽከርካሪዎችና መሳሪያዎች ብቻ የቴክኒክ ምርመራ ያስደረጉ፣ ቀሪዎቹ 48ቱ ደግሞ የአንድ ወይም የሁለት ዓመት ብቻ የቴክኒክ ምርመራ ያደረጉ መሆናቸው እየታወቀ ፈቃዳቸው የታደሰ መሆኑ ታውቋል፡፡

38. በተጨማሪም በኦዲቱ ወቅት በናሙና በተመረጡ ስራ ተቋራጮች የመስክ ጉብኝት ሲደረግ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለማውጣትና ለማሳደስ ሰነዶቻቸውን በማቅረብ የተጠቀሙባቸው ተሽከርካሪዎች እና መሳሪያዎች ለረጅም ጊዜ ተበላሽተው እና አገልግሎት መስጠት በማይችሉበት ሁኔታ እያሉ እንዲታደሱ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እድሳት ለማድረግ የሚመጡ ሥራ ተቋራጮች በሰነድ የሚያቀርቧቸው የሰው ኃይል ስራ ላይ መሆናቸው የማይረጋገጥ መሆኑ ታውቋል፡፡

39. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የብቃት ማረጋገጫ ለመውሰድ የመጡ የስራ ተቋራጮች መሳሪያና የሰው ሃይል ማሟላታቸውን በተመለከተ መሳሪያዎቹን ሚኒስቴር መ/ቤቱ በቼክ ሊስት መሰረት የሚያረጋግጥ መሆኑን፣ ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ የመንገድ ትራንስፖርት በሚሰጠው ዳታ ቤዝ በመጠቀም የሚሰራ በመሆኑ በአካል ተገኝቶ መመልከት /physical observation/ አስፈላጊ አለመሆኑን የገለፁ ሲሆን ሥራ ተቋራጮች ፈቃድ ለማውጣት ያስመዘገቧቸውን መሳሪያዎችና ተሽከርካሪዎች ማከራየትን በተመለከተ ሥራ በማይኖራቸው ወቅት ለኪሳራ እንዳይዳረጉ በማሰብ ማከራየት እንደሚችሉ በኢንቨስትመንት ቦርድ ታህሳስ 23 ቀን 2004 ዓ.ም በተወሰነው መሰረት ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ፈቃድ በመውሰድ ማከራየት እንደሚችሉ የተፈቀደላቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡

40. በእድሳት ወቅት ሥራ ተቋራጮች ፈቃድ ለማውጣት የተጠቀሙባቸው መሣሪያዎች በአካል መኖራቸውን በየጊዜው ከትራንስፖርት ባለስልጣን በሚመጣው ሶፍት ኮፒ እና ተገልጋዮች እራሳቸው ከሚመለከታቸው ትራንስፖርት ቢሮዎች በሚያመጧቸው ደብዳቤዎች የሚረጋገጥ መሆኑን፣ የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ሊብሬና ቦሎ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ተመርምሮ እንደሚሰራ፣ ከትራንስፖርት ባለስልጣንና ከክልሎች የሚመጣውን ግን ሠነድ ብቻ በማረጋገጥ የሚሠራ መሆኑን፣

የሰው ሃይሉን በተመለከተ ግን የተሰራ ሥራ አለመኖሩን፣ የገለጹ ሲሆን በተጨማሪም ሚኒስቴር መ/ቤቱን ሳያስታውቁ መሳሪያዎቻቸውን በኪራይ አገልግሎት ላይ የሚያውሉ ስራ ተቋራጮችን በተመለከት የተሰጠውን አስተያየት የተቀበሉት መሆኑንና በቀጣይነት እነዚህን ሥራዎች ለመቆጣጠርና ለመከታተል የሚያስችል ሥርዓት ተዘርግቶ በስራ ላይ እንዲውል የሚደረግ መሆኑን ለተላከላቸው ረቂቅ ኦዲት ሪፖርት በፅሁፍ በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

41. ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሥራ ተቋራጮች የብቃት ማረጋገጫ ፈቃዳቸውን ለማውጣት የሚያቀርቧቸው መሳሪያዎች መኖራቸውን በቼክ ሊስት መሰረት እንደሚያረጋግጥ ቢገልጹም ማስረጃው ባለመቅረቡ፣ የተሽከርካሪዎች እድሳትን በተመለከተ ከትራንስፖርት ባለሥልጣን በሶፍት ኮፒ ወቅታዊ /up-to-dated/ ተደርጎ እንደሚላክ የተገለፀው፣ መሳሪያዎች በእድሳት ወቅት መኖራቸው የተረጋገጠበት እና የስራ ተቋራጮች ያስመዘገቧቸው ስራተኞች ስራ ላይ መኖራቸውን በተመለከተ እንደ ማስረጃ የቀረቡት ሰነዶች ያልተሟሉና ምንጩ የማይታወቅ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

42. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሥራ ተቋራጮች ከቀረጥ ነፃ ያስገቧቸውና ፈቃድ ለማውጣት ያስመዘገቧቸው የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች፣ ተሽከርካሪዎችና የሰው ሃይል ዝርዝር በብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ ወቅትም ሆነ በእድሳት ወቅት በትክክል መኖራቸው ካልተረጋገጠ ያለ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፈቃድ መሣሪያዎችን ማከራየታቸው የዘርፉን የፈቃድ አሰጣጥ እና እድሳት አገልግሎት አሰጣጥ ለብልሹ አሰራሮች ተጋላጭ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

## ለሀገር በቀል ሥራ ተቋራጮች የሚደረገውን ድጋፍ በተመለከተ፣

43. ሚኒስትር መ/ቤቱ የሀገር በቀል የሥራ ተቋራጮች በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ውጤታማ እንዲሆኑ ሊደግፍ ይገባል፡፡

44. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ያለፉት ዓመታት ዕቅድ አፈጻጸም በሚገመገምበት ጊዜ፡-

- በ2006 ዓ.ም በመንገድ ዘርፍ የሚሳተፉ 28፣ በህይል ዘርፍ የሚሳተፉ 22 እንዲሁም በባቡር ዘርፍ የሚሳተፉ 20 በጥቅል የ70 ሥራ ተቋራጮች ቁጥር እንዲያድግ ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ አቅዶ ያላከናወነ እና ከ2007-በ2009 ዓ.ም እቅድ ውስጥ ያልተካተተ መሆኑ፣

- በ2008 ዓ.ም የኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ስራ ባለሙያዎች፣ ተቋራጮች፣ አማካሪዎች፣ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች እና አስፈፃሚዎች የአቅም ክፍተትና የድጋፍ ፍላጎት በዓይነትና በደረጃ የሚያሳይ ሁለት ጥናት ለማዘጋጀት አቅዶ 1 ወይም 50 ከመቶ የተከናወነ ሲሆን ቀሪውን በተመለከተ በ2009 ዓ.ም እቅድ ላይ ያልተካተተ መሆኑ፣
- የሥራ ተቋራጮችና አማካሪዎች የአቅም ክፍተት ለመለየት በሐምሌ ወር 2008 ዓ.ም የተደረገ ቅድመ ዳሰሳ ጥናት፣ እና በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ከሚሳተፉ አስፈጻሚ መስሪያ ቤቶች ውስጥ የስራ ተቋራጮችና አማካሪዎች ያሉባቸውን የአቅምና የገበያ ክፍተት የሚታይባቸውን የሥራ መደቦች ለመለየት በመስከረም ወር 2009 ዓ.ም የደሰሳ ጥናት መደረጉን የሚገልፁ ሁለት ጥናቶች በኦዲቱ ወቅት የቀረቡ ሲሆን ጥናቶቹ አዲስ አበባ ባሉ ስራ ተቋራጮችና አስፈፃሚ አካላት ላይ የተሰራና በረቂቅ ደረጃ ያለ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

45. በተጨማሪም በ2009 በጀት ዓመት በአንደኛው ሩብ አመት እቅድ አፈጻጸም ላይ፡-

- ለአመቱ 300 ነባር ስራ ተቋራጮች የሚደገፉበትን ስልት በመቀየስ ደረጃቸው ከፍ እንዲል ድጋፍና ክትትል ለማድረግ ከታቀደው ውስጥ በመጀመሪያው ሩብ ዓመት በቁጥር 37 ለማከናወን ቢያታቀድም ያልተከናወነ መሆኑ፣
- በበጀት አመቱ በዓመቱ መጨረሻ 1,200 የሥራ ተቋራጮችን የገበያ ክፍተት የሚታይባቸውን መስኮች በደሰሳ ጥናት በመለየት ታቅዶ፣ በመጀመሪያው ሩብ ዓመት በ149 ድጋፍና ክትትል ማድረግን አቅዶ 34 (22.8 በመቶ) ብቻ ያሳደገ መሆኑ፣
- በበጀት አመቱ በዓመቱ መጨረሻ 900 በተለዩ የሥራ መስኮች አዲስ የስራ ተቋራጮች ወደ ስራ እንዲገቡ ድጋፍና ክትትል ማድረግ ታቅዶ በአንደኛ ሩብ ዓመት ደግሞ 112 ቢታቀድም 34 (30.35 በመቶ) ብቻ የተከናወነ መሆኑን፣

ለማወቅ ተችሏል፡፡

46. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ይህንን ተግባር ለመስራት ኃላፊነት የተሰጠው የኮንስትራክሽን ኩባንያዎች ልማት፣ አቅም ግንባታና ተወዳዳሪነት ማበልፀጊያ ዳይሬክቶሬት በ2008 እና 2009 ዓ.ም ሁለት ጥናቶች ማለትም የስራ ተቋራጮችና አማካሪዎች የአቅም ክፍተት ለመለየት የተደረገ ቅድመ ዳሰሳ ጥናት መደረጉንና ጥናቱም እንደ አዲስ አበባ ቢደረግም እንደ ክልል ግን የሚቀሩ ነገሮች እንዳሉት የገለጹ ሲሆን በእቅዱ ላይ የተገኙ ነገሮች በተመለከተ ሚኒስቴር መ/ቤቱ አዲስ በመሆኑ፣ አደረጃጀቱ ባለመጠናቀቁና የሰው ኃይል ባለመሟላቱ ሊሰሩ አለመቻላቸውን በተላከላቸው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (Fact Sheet) ላይ በሰጡት አስተያየት የገለፁ ሲሆን በተጨማሪም ለተላከላቸው ረቂቅ ኦዲት ሪፖርት በጽሁፍ በሰጡት ምላሽ በኦዲት ግኝቱ ላይ የተጠቀሱትን መቀበላቸውንና በቀጣይ ግን በነሐሴ 2008 ዓ.ም አገር አቀፍ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ የአቅም ግንባታ ፕሮግራም ማዕቀፍ ረቂቅ ሰነድ በማዘጋጀት ለሚመለከተው አካል እንዲቀርብ ማድረጋቸውን ገልፀዋል፡፡

47. ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ የተዘጋጀው ረቂቅ ሠነድ ለሚመለከተው አካል የተላከ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ባለመቅረቡ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

48. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሥራ ተቋራጮች ዙሪያ በሚታዩ ችግሮች ላይ የተለያዩ ጥናቶችን በማጥናት ተግባራዊ እንዲሆኑ አለማድረጉ ያሉባቸው ክፍተቶች በጊዜው እንዳይሟላ፣ ችግሮቻቸው በወቅቱ መፍትሄ እንዳያገኙ እና በገበያው ላይ ተወዳዳሪ እንዳይሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡

**ሥራ ተቋራጮች በየፕሮጀክቶቻቸው የሚያሰማሯቸው ሠራተኞችን በተመለከተ፣**

49. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ተቋራጮች በየፕሮጀክቶቻቸው የሚያሰማሯቸው ሠራተኞች የብቃት ደረጃ ከሚያሠሯቸው ተግባር ጋር ተመጣጣኝ መሆኑን የሚያረጋግጥበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግና ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

50. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ተቋራጮች በየፕሮጀክቶቻቸው የሚያሰማሯቸው ሠራተኞች የብቃት ደረጃ ከሚወስዱቸው የግንባታ ኮንትራቶች እና ሰራተኞቹን ከሚያሠሯቸው ተግባር ጋር ተመጣጣኝ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

51. ስለ ሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ይህን ተግባር ለማከናወን ኃላፊነት ያለበት ክፍል በሰው ኃይልና በመሳሪያ የተደራጀ ባለመሆኑ ስራው ሊሰራ አለመቻሉን ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም በኦዲቱ የተሰጠውን አስተያየት የተቀበሉና ለወደፊት የሚመዘገቡ ባለሙያዎችን ቁጥጥር ሥርዐት ተዘርግቶ ተግባራዊ ለማድረግ ጥረት የሚደረግ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

52. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሥራ ተቋራጮች በየፕሮጀክቶቻቸው የሚያሰማሩአቸውን ሠራተኞች የብቃት ደረጃ ከሚያሰሯቸው ተግባር ጋር ተመጣጣኝ መሆኑን በየጊዜው አለማረጋገጡ የሚፈፀሙ ግንባታዎች ሙያው እና እውቀቱ በሌላቸው አካላት እንዲከናወኑና ስራው የጥራት መጓደል እንዲያጋጥመው ያደርጋል፡፡

## ለአገር ውስጥ ሥራ ተቋራጮች የሚሰጡ ሥልጠናዎችን በተመለከተ፣

53. ለአገር ውስጥ የሥራ ተቋራጮች የተለያዩ ሥልጠናዎችን በመስጠት ደረጃቸውን እንዲያሳድጉ በማመቻቸት ብቃታቸው እንዲጨምር የሚያደርግበት የአሠራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

54. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው የተጠየቁም ሆነ ሰነዳቸው የተከለሰ የስራ ተቋራጮች ከሚኒስቴር መ/ቤቱ (ከቀድሞው የከተማ ልማት፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር) ጭምር ምንም ዓይነት  የአቅም ግንባታ ድጋፍ /ስልጠና/ አግኝተው  የማያውቁ መሆኑን የገለጹ ሲሆን የሚኒስቴር መ/ቤቱ ዕቅድ አፈጻጸም በሚከለስበት ወቅት፡-

- በ2008 ዓ.ም ዕቅድ አፈጻጸም ላይ ለ1,000 ስራ ተቋራጮች ስልጠና ለመስጠት አቅዶ ለሁሉም የተሰጠ መሆኑ በእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ የተገለጸ ቢሆንም ለኦዲቱ ሥልጠና የተሰጠበት ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፣
- በ2008 ዓ.ም እቅድ ላይ ለ400 አዲስ ስራ ተቋራጮች የስልጠና ድጋፍ እና የፋይናንስ አቅርቦት በማመቻቸት በዘርፉ እንዲሰማሩ ለማድረግ ቢያቅድም ያልተከናወነ ሲሆን በ2009 በጀት አመት ለአቅም ግንባታ ስራዎች ለ3150 ሥራ ተቋራጮች እና ለልማት ሥራዎች ለ2328 ሥራ ተቋራጮች ስልጠና ለመስጠት ቢያቅድም እስከ አንደኛው ሩብ ዓመት ድረስ ስልጠናው ያልተሰጠ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

55. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በቂ ባይሆንም ለሥራ ተቋራጮች ስልጠናዎች መሰጠታቸውን ገልፀው እንደ ማስረጃም ከ2007 -2009 ዓ.ም ድረስ ለስራ ተቋራጮችና አማካሪዎች የተሰጡ የስልጠና ዓይነቶች ዝርዝር ያቀረቡ ሲሆን በእቅድ ተይዘው ያልተሰጡ ስልጠናዎችን በተመለከተ ምንም ዓይነት ምላሽ አልሰጡም፡፡ በተጨማሪም ከታህሳስ 17-28/2009 ISO 9001 -2015 ለሥራ ተቋራጮች፣አማካሪዎችና ለኮንስትራክሽን መሳሪያዎች አምራች፣ አቅራቢ፣ አከራይና ጠጋኝ ድርጅቶች ስልጠና መሰጠቱን የሚያሳይ ማስረጃ ለረቂቅ ኦዲት ሪፖርቱ በፅሁፍ ከሰጡት ምላሽ ጋር አያይዘው አቅርበዋል፡፡

56. ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ ለሥራ ተቋራጮችና አማካሪዎች ተሰጡ የተባሉት የስልጠና ዓይነቶች እንጂ ለምን ያህል ስራ ተቋራጮች ስልጠናው እንደተሰጠ ለማወቅ የሚያስችል ማስረጃ ሊቀርብ ባለመቻሉ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

57. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ተቋራጮችን አቅም ለማጎልበት የሚረዱ የተለያዩ ስልጠናዎችን በእቅዱ መሰረት አለመስጠቱ ያሉባቸውን የአቅም ውስንነት በወቅቱ በማጎልበት ወደ ተሻለ ደረጃ እንዳይደርሱ በማድረግ በዘርፉ በሚኖራቸው እድገትም ሆነ ተወዳዳሪነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡

## ፈቃድ የወሰዱ ሥራ ተቋራጮች በየዓመቱ ማሳደሳቸውን መቆጣጠርና መከታተልን በተመለከተ፣

58. ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ፈቃድ የወሰዱ ሥራ ተቋራጮች በየዓመቱ ፈቃድ ያሳደሱ መሆናቸውን ሊከታተልና ሊቆጣጠር፣ ያላሳደሱትን በተቋራጭነት ሥራ ላይ እንዳይሰማሩ ለማድረግ ህብረተሰቡ፣ የግል ድርጅቶች፣ የመንግስት ተቋማት እና የሚመለከታቸው አካላት እንዲያውቁት የሚደረግበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡

59. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፌዴራል ደረጃ ፈቃድ የወሰዱ ሥራ ተቋራጮች በየዓመቱ ፈቃዳቸውን ማደሳቸውን የማይከታተልና የማይቆጣጠር በመሆኑ እስከ 2008 ዓ.ም ድረስ ከ11,912 ስራ ተቋራጮች ውስጥ 5,321 ስራ ተቋራጮች ፈቃድ ያላሳደሱ ሲሆን ህብረተሰቡ፣ የግል ድርጅቶች፣የመንግስት ተቋማት እና የሚመለከታቸው ዋና ዋና ባለድርሻ አካላት እንዲያውቁት ያላደረገ መሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡

60. ስለ ሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ሥራ ተቋራጮች በየዓመቱ ፈቃዳቸውን ባያሳድሱ የተለያዩ ጨረታዎችም ሆነ ስራዎች ላይ ያሳደሱበትን ማስረጃ የሚጠየቁና ከሌላቸው መሳተፍ እንደማይችሉ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚያውቅ በመሆኑ አለማሳደሳቸውን እንደ ጥያቄ እንደማያቀርብና እንደማይገደዱ፣ ፈቃዳቸውን ያሳደሱ ስራ ተቋራጮች በቀድሞው ከተማ ልማት ሚኒስቴር ዌብ ሳይት ይለቀቅ የነበረ መሆኑን ነገር ግን ያላሳደሱትንም አብሮ በመልቀቅ ህብረተሰቡ፣ የግል ድርጅቶች፣ የመንግሥት ተቋማት እና የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት እንዲያውቁት አለመደረጉ ሚኒስቴር መ/ቤቱ እንደ ችግር ወስዶ ሊቀርፈው የሚገባ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

61. በተጨማሪም ለተላከላቸው ረቂቅ ኦዲት ሪፖርት በፅሁፍ በሰጡት ምላሽ በየአመቱ ፈቃድ የሚያወጡ ሥራ ተቋራጮች ከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ዌብ ሳይት ላይ በ15ቀኑ ወቅታዊ መረጃን መሰረት በማድረግ የሚለቀቅ ሲሆን በዚያ ዝርዝር ውስጥ ያልተካተቱ ሥራ ተቋራጮች በመንግስት ግንባታ ሥራዎች ላይ እንዳይሳተፉ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱን ነገር ግን ይህ መረጃ በቂ ሊሆን ስለማይችል በቀረበው የኦዲት አስተያየት መሰረት በዌብ ሳይት ላይ ፈቃዳቸውን ያደሱና ያላሳደሱትንም ጭምር ለማውጣት የሚያስችል ስርዓት እንደሚዘረጋ እንዲሁም የሥራ ተቋራጭነት ፈቃድና ምዝገባ የንግድ ሥራ ፈቃድ በመሆኑ የኩባንያ ባለቤቶች ፈቃድ እንዲያድሱ ማስገደድ ወይም እየተከታተሉ እንዲያድሱ ማድረግ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚጠበቅ ስራ እንዳልሆነ ገልፀዋል፡፡

62. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎቹ ይህን ምላሽ ይስጡ እንጂ በ 2006 ዓ.ም በተዘጋጀው የኮንስትራክሽን የባለሙያዎችና የስራ ተቋራጮች ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 19 ላይ በየአመቱ መታደስ ያለበት እና ያልታደሰ ፈቃድ በወቅቱ መሰረዝ ያለበት በመሆኑ፣ ፈቃድ መታደሱንና አለመታደሱን ሳይጠይቁ ኮንትራት የሚሰጡ አካላት ሊኖሩ ስለሚችሉ እንዲሁም የሥራ ተቋራጮቹ ፈቃዳቸውን ሳያሳድሱ እንደማይሰሩ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ማረጋገጥ ስለነበረበት እና የንግድ ፈቃድ እና የሥራ ተቋራጮች ፈቃድና ምዝገባ የተለያዩ በመሆናቸው ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚጠበቅ ተግባር ስለሆነ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

63. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፌዴራል ደረጃ የተመዘገቡ ሥራ ተቋራጮች በየዓመቱ ፈቃዳቸውን ማሳደሳቸውን አለመከታተሉ እና ያላሳደሱትን ፈቃድ አለመሰረዙ በህገወጥ መልክ የሚሰማሩ የሥራ ተቋራጮች እንዲኖሩ ያደርጋል፡፡

## በሥራ ተቋራጮች በመገኘት የሚደረግን ድንገተኛ ጉብኝት በተመለከተ፣

64. ፈቃድ የወሰዱ የሥራ ተቋራጮች ያስመዘገቧቸው (የሰው ኃይል፣ መሳሪያዎችና ተሽከርካሪዎች) ፈቃድ ለወሰዱበት ሥራ እየዋሉ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል (በስራ ቦታው ላይ ድንገተኛ ጉብኝት በማድረግ የተመዘገቡት መሳሪያዎች በስራ ላይ ስለመሆናቸው) በየአመቱ እቅድ በማዘጋጀት የሚጣራበት የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

65. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በአካል የታዩ እና ሰነዳቸው የተከለሰ ሥራ ተቋራጮች ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ፈቃድ ሲያወጡ ያስመዘገቡአቸው የሰው ኃይል፣ መሳሪያዎች እና ተሽከርካሪዎች ለወሰዱት ዓላማ መዋሉን በሚኒስቴር መ/ቤቱ የክትትልና ቁጥጥር ሥራ ያልተሰራ መሆኑን የገለጹ ሲሆን የሚኒስቴር መ/ቤቱ ዕቅድ አፈጻጸም በሚከለስበት ወቅት፡-

- በ2008 በጀት አመት ለ1,605 የሥራ ተቋራጮች እና የአማካሪ ድርጅቶች የኢንስፔክሽን ሥራ ለመስራት አቅዶ ለ1,622 ማለትም 101 በመቶ የተከናወነ መሆኑ ቢገልፅም ማስረጃው ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ባለመቅረቡ ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፣
- በ2008 ዓ.ም በደረጃ አንድ ለተሰማሩ 160 ሥራ ተቋራጮች የሠራተኞችን ደህንነት መጠበቂያ እና መከላከያ አልባሳትና መሣሪያዎችን እንዲያሟሉ ክትትል ለማድረግ ታቅዶ ያልተከናወነ ሲሆን፣ በ2009 በጀት ዓመት በ1000 የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች ላይ ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ እቅድ የተያዘ ሲሆን በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያው ሩብ ዓመት ደግሞ 86 ፕሮጀክቶች ላይ ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም ያልተከናወነ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

66. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በኦዲት ግኙቱ የተቀመጡ ነገሮችን እንደክፍተት የሚወስዱትና የሚቀበሉት መሆኑን በቀጣይ የስራ ተቋራጮችን ለመቆጣጠርና ክትትል ለማድረግ የአሰራር ስርዓት ለመዘርጋት ጥረት የሚደረግ መሆኑን ለረቂቅ ኦዲት ሪፖርት በፅሁፍ በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

67. ሥራ ተቋራጮች ከቀረጥ ነፃ አስገብተው የብቃት ማረጋገጫ ለማውጣት የተጠቀሙባቸው መሳሪያዎችና ተሽከርካሪዎች ሥራ ላይ መኖራቸውን በድንገት በስራ ቦታቸው በመገኘት ቁጥጥር አለማድረጉ መሳሪያዎች/ተሽከርካሪዎችን ለሌላ አላማ የሚያውሉ ስራ ተቋራጮች ቁጥር በየጊዜው እንዲጨምር ያደርጋል፡፡

**የመሳሪያዎች/ ተሽከርካሪዎች ዝርዝር መረጃዎች ወቅታዊ የሚደረጉበት ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ሥርዓትን በተመለከተ፣**

68. በአንድ መሳሪያ ብዛት ያላቸው የሥራ ተቋራጮች ፈቃድ እንዳያወጡ ለማድረግ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ተቋራጮች ፈቃድ ለማውጣት እና ለማሳደስ የሚያስመዘግቧቸውን የመሳሪያዎች/ ተሽከርካሪዎች ዝርዝር መረጃ የባለቤትነት ደብተር እና ሌሎች ተያያዥ ሁኔታዎች የሚሳዩ መረጃዎች የሚመዘገብበትና ወቅታዊ የሚደረጉበት ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

69. ይሁን እንጂ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች/ ተሽከርካሪዎች ዝርዝር መረጃ የባለቤትነት እና ሌሎች ተያያዥ ሁኔታዎች የሚያሳዩ መረጃዎች የሚመዘገብበትና ወቅታዊ የሚደረግበት ዘመናዊ መረጃዎች አያያዝ ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡ በተጨማሪም የሥራ ተቋራጮች የሚያቀርቧቸው ሊብሬዎች እና የመኪና ሽያጭ ውል ወይም ዲክላሬሲዮን 3ኛ ወገን እና ተያዥ ሰነዶችን ሲያቀርቡ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ትክክለኛነቱን ፈቃድ ሲያወጡ ያቀረቡትን ተሽከርካሪ በእድሳት ወቅት ሲያመጡ አጠራጣሪና ሐሰተኛ ሆነው ሲገኙ የማያጣራ መሆኑ፣ በአንድ የኮንስትራክሽን ማሽነሪ/ ተሽከርካሪ በድጋሚ ሌሎች ፈቃድ እንዳያወጡ ለማጣራት የሚያስችለው የአሰራር ሥርዓት ያልዘረጋ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

70. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ በመረጃ አያያዝ ዙሪያ የተነሱት ነገሮች ትክክል መሆናቸውን ነገር ግን ሚኒስቴር መ/ቤቱ እራሱን ችሎ ከወጣበት ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ የራሱን ፖርታል እያዘጋጀ በመሆኑ እና በመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በኩል ኢ-ሰርቪስ ከፖርታል ጋር የማገናኘት ሂደቱ በመዘግየቱ የተጠቀሰው ሥራ ሊከናወን አለመቻሉን ገልፀዋል፡፡

71. የሥራ ተቋራጮችን የሚመለከቱ መረጃዎችን ወቅታዊነቱን በጠበቀና ዘመናዊ በሆነ መልኩ መረጃዎችን አለመያዙ ሐሰተኛ ሰነዶች እንዲበራከቱና በአንድ መሳሪያ

ብዛት ያላቸው የሥራ ተቋራጮች ፈቃድ እንዳያወጡ ለማድረግ በር ከመክፈቱም በላይ የክትትልና ቁትጥር ሥርዓቱን አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡

## ከተሠጣቸው ደረጃ ውጭ የሚሰሩ የሥራ ተቋራጮችን በተመለከተ፣

72. የሥራ ተቋራጮች በተሰጣቸው ደረጃ ሊሠሩ የሚገባቸውን ግንባታ ብቻ ሊሰሩ ይገባል፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱም ከተሠጣቸው ደረጃ ውጭ የሚሰሩ የሥራ ተቋራጮች እንዳይኖሩ ለመከላከል የሚያስችል የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

73. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከተሠጣቸው ደረጃ ውጭ የሚሰሩ የሥራ ተቋራጮች እንዳይኖሩ ለመከላከል የሚያስችል የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አለማድረጉ ታውቋል፡፡

74. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከተሰጣቸው ደረጃ ውጭ የሚሰሩ ስራ ተቋራጮች እንዳይኖሩ ለመከላከል የሚያስችል የቁጥጥር ስርዐት ዘርግቶ ተግባራዊ ያላደረገ ሲሆን ችግሮች ሲከሰቱ ብቻ የማገድ እርምጃ እንደሚወስድ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩ 17 የታገዱ ፋይሎች/ሰነዶች ውስጥ በ6ቱ ከኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ካወጡት የፈቃድ ደረጃ በላይ ይሰሩ የነበሩ፣ በተለያዩ ደረጃዎች ሁለት የብቃት ማረጋገጫዎችን ያወጡ፣ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የብቃት ማረጋገጫ ከማውጣታቸው በፊት በህገ-ወጥ የብቃት ማስረጃ በፈለጉት የደረጃ አይነት ላይ ሲሰሩ የነበሩ በነበሩ ስራ ተቋራጮች አማካይነት ለማወቅ ተችሏል፡፡

75. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በኦዲት ግኝቱ ላይ የተጠቀሱት ነገሮች ተቀባይነት እንዳለውን በቀጣይ ይህንን ችግር ለመቅረፍ የሚያስችል የቁጥጥር ስርዓት ተዘርግቶ የሥራ ተቋራጮች በተመዘገቡበት የሥራ ደረጃ ብቻ እንዲሰሩ ለማድረግ ተገቢውን ጥረት እንደሚደረግ ለረቂቅ ኦዲት ሪፖርት በፅሁፍ በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

76. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከተሠጣቸው ደረጃ ውጭ የሚሰሩ የሥራ ተቋራጮች እንዳይኖሩ ለመከላከል የሚያስችል የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አለማድረጉ ከአቅማቸው በላይ ሕገ-ወጥ ሰነዶችን በመያዝ ትላልቅ ኮንትራክቶችን ያለደረጃቸው በመውሰድ ትክክለኛ ደረጃ ያላቸው የሥራ ተቋራጮች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ከማሳደሩም በላይ የሚሰራውም ግንባታ ጥራትም አጠራጣሪ ያደርገዋል፡፡

**ፈቃዳቸውን ለሌላ አካል አሳልፈው የሚሰጡ የስራ ተቋራጮችን በተመለከተ፣**

77. የሥራ ተቋራጮች በወሰዱት ፈቃድ ብቻ ሊሰሩ ይገባል፡፡ የሚኒስቴር መ/ቤቱም ፈቃዳቸውን ለሌላ አካል አሳልፈው የሚሰጡ የስራ ተቋራጮች የሚጠየቁበት የአሰራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
78. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፈቃዳቸውን ለሌላ አካል አሳልፈው የሚሰጡ የሥራ ተቋራጮች እንዳይኖሩ ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚያስችል ስልት አልተዘጋጀም፡፡
79. ይህን በተመለከተ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ምንም የተዘረጋ ሥርዓት አለመኖሩንና በኦዲት ግኝቱ ላይ የተጠቀሱ ነገሮች የሚቀበሉ መሆኑን በቀጣይ ይህን ተገቢ ያልሆነ አሰራር ለመከላከል በአገር አቀፍ ደረጃ ወጥ የሆነ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ የሚደረግ መሆኑን ለረቂቅ ኦዲት ሪፖርት በፅሁፍ በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡
80. ፈቃዳቸውን ለሌላ አካል አሳልፈው የሚሰጡ የስራ ተቋራጮች ሊጠየቁበት የሚችሉበት ሥርዐት በመዘርጋት ተግባራዊ አለመደረጉ በተለያዩ የፕሮጀክት ስራዎች የሚከሰቱ ችግሮች ላይ ተጠያቂ የሚሆነውን አካል በመለየት ተገቢው እርምጃ እንዳይወሰድበት ከማድረጉም በላይ ብቃታቸው ሳይረጋገጥ በግንባታ ሥራ ላይ በሚሰማሩ አካላት ህብረተሰቡ እንዲጭበረበር ያደርጋል፡፡

**የሥራ ተቋራጮች የአገልግሎት መስጫ የጊዜ ገደብና የተገልጋዮች ፍላጎት እርካታን በተመለከተ፣**

81. ለሥራ ተቋራጮች የሚሰጡ አገልግሎቶች በተቀመጠው የአገልግሎት መስጫ የጊዜ ገደብ መሰረት አገልግሎት ፈላጊዎች ሊስተናገዱ ይገባል፡፡ ተገልጋዮችንም ለማስተናገድ የሚያስችል የሥራ አካባቢ ሊያመቻች ይገባል፡፡ የተገልጋዮችን ፍላጎት እርካታን ለማወቅና ክፍተቶቹን እየገመገመ ለማስተካከል የሚያስችል ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግና በየጊዜው ማስተካከል አለበት፡፡
82. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለሥራ ተቋራጮች የሚሰጡ አገልግሎቶች በጊዜ ገደብ መሆን እንዳለባቸው በመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት BPR ሰነድ ላይ ለአዲስ ምዝገባ 1፡45 ሰዓት፣ እድሳት 1፡32 ሰዓት፣ የደረጃ/የዘርፍ ለውጥ 1፡32 ሰዓት የጠፋ ብቃት ማረጋገጫ ምትክ ጥያቄ 0.65 ሰዓት፣ ፈቃድ ስረዛ ፈቃድ

የወሰደው አካል ሲመለስ 0.28 ሰዓት እና በቅጣት ሲሰረዝ 0.41 ሰዓት አገልግሎት ለመስጠት የጊዜ ተመን ያስቀመጠ ቢሆንም ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑን ታውቋል፡፡

83. በተጨማሪም

- በ2008 ዓ.ም በዘርፉ ለተሰማሩ ባለሙያዎች፣ ሥራ ተቋራጮች፣ አማካሪዎች እና የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች ምዝገባ እና የፈቃድ አሰጣጥ የon-line አገልግሎት በመስጠት 80 በመቶ ተግባራዊ ለማድረግ፣ ቢያቅድም ያላከናወነ ሲሆን በ2009 በጀት ዓመት እቅድ የተያዘ ቢሆንም እስከ አንደኛው ሩብ ዓመት ድረስ ያልተከናወነ መሆኑ፣
- በ2008 ዓ.ም የኮንስትራክሽን ምዘገባ የአገልግሎት አሰጣጥ ሥርአትን በአውቶሜሽን ቴክኖሎጂና (Back Office Automation) የተደገፈ እንዲሆን ቢያቅድም ያላከናወነና በ2009 በጀት ዓመት እቅድ የተያዘ ቢሆንም እስከ አንደኛ ሩብ ዓመት ድረስ ያልተከናወነ መሆኑን፣

ለማወቅ ተችሏል፡፡

84. በተጨማሪም ሚኒስቴር መ/ቤቱ፡-

- በ2007 ዓ.ም የተገልጋይ ዕርካታ የመመዘኛ መስፈርቱን አዘጋጅቶ በማጸደቅ አስተያየት ለመሰብሰብና ለመመዘን ቢያቅድም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ያልተከናወነ መሆኑ፣ እና በ2008 በጀት አመት እቅድ ውስጥ ያልተካተተ ሲሆን በ2009 በጀት ዓመትም የተገልጋይ እርካታን 90 በመቶ ለማድረስ በእቅድ የያዘና ከእቅዱ ውስጥ በአንደኛ ሩብ ዓመት አንድ የፀደቀ የተጋልጋይ የመመዘኛ መስፈርት ለማዘጋጀት አቅዶ ያላከናወነ መሆኑ፣
- በ2008 ዓ.ም የስራ ተቋራጭ የአማካሪዎች፣ ባለሙያዎችና የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች ምዝገባ ተገልጋዮች የአገልግሎት እርካታ 80 ከመቶ ለማድረስ አቅዶ 69 ከመቶ ማድረሱን በክንውኑ ላይ ቢገልጽም ማስረጃው ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ያልቀረበ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

85. በኦዲቱ ወቅት በናሙና የታዩት ስራ ተቋራጮች የሚኒስቴር መ/ቤቱ የአገልግሎት አሰጣጥ ላይ እርካታ የሌላቸው መሆኑን የገለፁ ሲሆን ተገልጋዮች ከሚኒስቴር

መ/ቤቱ የተለያዩ አገልግሎቶችን ለማግኘት ሲመጡ የሚስተናገዱበት የተገልጋይ ማረፊያ የሌለና በቢሮው አካባቢ በሚገኙ ዛፎች ጥላ ስር እንዲቆዩ የሚገደዱ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ለማየት ተችሏል፡፡

86. ስለ ሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በቀድሞው ከተማ ልማት ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በ2006 ዓ.ም በተዘጋጀው በመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ (BPR) ጥናት ላይ ለሥራ ተቋራጮች የሚሰጡ የተለያዩ አገልግሎቶች የጊዜ ገደብ የተቀመጠላቸው እንደሆነና የሰው ሃይል እጥረት፣ የቢሮ አቀማመጥ ምቹ አለመሆን እና የback office automation ተግባራዊ ባለመሆኑ በጥናቱ መሰረት ወደ ተግባር መግባት አለመቻሉን፣ የተገልጋዮችን ፍላጎትና እርካታን ለማወቅና ክፍተቶቹን እየገመገመ ለማስተካከል የሚያስችል የአሰራር ሥርዓትም አለመዘርጋቱን የገለፁ ሲሆን ለተላከላቸው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ /Fact sheet/ በሰጡት አስተያየት ላይ በመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ (BPR) ጥናት ላይ ለሥራ ተቋራጮች የሚሰጡ የተለያዩ አገልግሎቶች በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ መስጠትን ተግባራዊ አለማድረግን በተመለከተ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጥናቱን ከዚህ በፊት እንዳላጠና እና ለማዘጋጀት ገና በሂደት ላይ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

87. ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ በቀድሞ የከተማ ልማት፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ጥር 2006 ዓ.ም የተጠናው የመሰረታዊ አሰራር ሂደት ለውጥ ላይ የተቀመጠውን የአገልግሎት መስጫ ጊዜ አዲስ እስኪዘጋጅ መጠቀም ይቻል ስለነበረ እና ይህንኑ ጥናት ሌሎች የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ክፍሎች እየተጠቀሙበት በመሆኑ የሰጡትን ምላሽ አልተቀበልነውም፡

88. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሥራ ተቋራጮች የሚፈልጓቸው አገልግሎቶች ለአገልግሎት በተቀመጡት ሰዓቶች አለመስጠቱና ከተገልጋዮች አገልግሎት አሰጣጡ ላይ የሚነሱ ፍላጎቶችን/ቅሬታዎችን በየጊዜው በመለየትና በመገምገም ማስተካከያ የሚያደርግበት የአሰራር ስርአት አለመዘርጋቱና ተገልጋዮች የሚስተናገዱበት ምቹ አካባቢ አለመዘጋጀቱ ተገልጋዮችን አስፈላጊ ላልሆነ እንግልት፣ የገንዘብና የጊዜ ብክነት እንዲጋለጡ እና ያጋጠሟቸው ችግሮች በወቅቱ ማስተካከያ እንዳያገኙ ያደርጋል፡፡

**ለመንግስትና ለህዝብ አገልግሎት በሚውሉ ግንባታዎች ላይ የሚደረግ የክዋኔ ኦዲትን በተመለከተ፣**

89. ለመንግስትና ለህዝብ አገልግሎት የሚውሉ ግንባታዎች ከተጠናቀቁና የመጨረሻ ርክክብ ከተፈጸመ በኋላ የግንባታውን ሂደት ለማወቅ የክዋኔ ኦዲት የሚከናወነበት የአሰራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

90. ይሁን እንጂ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የዕቅድ አፈጻጸም በሚከለስበት ወቅት ክዋኔ ኦዲት የሚደረግባቸውን የግንባታ ፕሮጀክቶች ለመለየት፣ ለመንግስትና ለህዝብ አገልግሎት የሚውሉ ግንባታዎች ከተጠናቀቁና የመጨረሻ ርክክብ ከተፈጸመ በኋላ የግንባታውን ሂደት ለማወቅ የክዋኔ ኦዲት ለማከናወን እንዲሁም የፕሮጀክቶችን ውጤታማነት (value for money) ለማረጋገጥ የሚረዳ 1 ማንዋል ለማዘጋጀት በ2008 እና በ2009 በጀት ዓመታት በዕቅድ ቢይዝም ማንዋሉ ያልተዘጋጀና ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ አንድም ኦዲት አለማከናወኑ ታውቋል፡፡

91. ስለ ሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በኦዲት ግኝቱ የተጠቀሱ ነገሮችን የተቀበሉት መሆኑን ለረቂቅ ኦዲት ሪፖርት በፅሁፍ በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

92. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በየዓመቱ ግንባታቸው የተጠናቀቁ የመንግስት ግንባታዎችን በናሙና መርጦ የክዋኔ ኦዲት አለመስራቱ ቀድሞ በተሰሩ ፕሮጀክቶች ግንባታ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችም ሆነ መልካም አፈፃፀሞች አዲስ ሊሰሩ/ሊጀመሩ ለሚታሰቡ ሌሎች ፕሮጀክቶች ግብአት እንዳያገኙ ያደርጋል፡፡

**የፌዴራልና የክልሎች የኮንስትራክሽን ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ ተመሳሳይ ስታንዳርድ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፣**

93. በፌደራል እና በክልሎች ያለው በየደረጃው የሚከናወነው የስራ ተቋራጮች ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ ተመሳሳይ ስታንዳርድ እንዲኖረው ለማድረግ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት እንዲዘረጋ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ሊሰራ ይገባል፡፡

94. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፌደራል እና በክልሎች ያለው በየደረጃው የሚከናወነው የስራ ተቋራጮች ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ ተመሳሳይ ስታንዳርድ ያለው ቢሆንም ተግባራዊነቱ ላይ ልዩነት ያለው መሆኑን በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩ ከኦሮሚያ ኮንስትራክሽን ቢሮ እና በአዲስ አበባ አስተዳደር ኮንስትራክሽን ቢሮ ለመረዳት ተችሏል

95. ስለ ጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በሁሉም ክልሎች የሚሰጠው ምዝገባ በፌዴራል በወጣው መመሪያ መሰረት እንደሆነ አተገባበር ላይ ግን ተመሳሳይ ሊሆን እንደማይችል፤ በጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ተደራጅተው ለሚቀርቡ እንደ የክልሉ ሁኔታ የየራሳቸውን መስፈርት በማውጣት በደረጃ 8፣ 9 እና 10 ላይ የብቃት ማረጋገጫ እንደሚሰጡ እና ሁለትና ከዛ በላይ በሆኑ ክልሎች ውስጥ የሚሰሩ ስራ ተቋራጮች ፈቃዳቸውን ከፌዴራል ማውጣት ያለባቸው መሆኑን በአዋጁ በመደንገጉ ምክንያት መሆኑን ገልፀዋል፡፡

96. በፌዴራልና በክልል የሚከናወነው የምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ ሂደት ተመሳሳይ አለመሆኑ ፈቃዱን በሚወስዱ ተገልጋዩች መካከል ቅሬታ እንዲፈጠር ከማድረጉም በላይ በአገልግሎት አሰጣጡም ላይ ችግር ሊስከትል ይችላል፡፡

### 2.1.2 ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው የመንግስት መ/ቤቶች እና ባለድርሻ አካላት ጋር የሥራ ተቋራጮችን ውጤታማ ለማድረግ እና ለመደገፍ በቅንጅት የሚሰሩበት አሰራር መዘርጋቱንና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፣

**ከባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ የሚደረግ ቁጥጥርና ክትትልን በተመለከተ፣**

97. ሚ/ር መ/ቤቱ ከክልል የኮንስትራክሽን ዘርፍ ተቋማት እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት (የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ መንገድ ትራንስፖርት፣ የሙያ ማህበራት፣ ኢንሹራንስ….ወዘተ) ጋር በመቀናጀት መከታተል የሚያስችል ቼክ ሊስትና የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ስራ ተቋራጮች በተሰጣቸው የብቃት ማረጋገጫ መሰረት እየሰሩ መሆናቸውን ቁጥጥርና ክትትል ሊያደርግ እና በክትትሉ መሰረት የፅሁፍ ግብረ መልስ ሊሰጥ ይገባል፡፡

98. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልል የኮንስትራክሽን ዘርፍ ተቋማት እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት (የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን፣ መንገድ ትራንስፖርት፣ የሙያ ማህበራት፣ ….ወዘተ) ጋር በመቀናጀት የድርጊት መርሃ ግብር በማውጣት ስራ ተቋራጮች በተሰጣቸው የብቃት ማረጋገጫ መሰረት እየሰሩ መሆናቸውን በመከታተል ቁጥጥርና ክትትል በማድረግ ግብረ-መልስ ያልሰጠ መሆኑ ታውቋል፡፡

99. ስለ ሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በኦዲት ግኝቱ ላይ የተሠጠውን አስተያየት የሚቀበሉት መሆኑን በቀጣይ ከሚመለከታቸው የባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመስራት እና የስራ ተቋራጮችን አፈፃፀም ለመገምገም የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ለማድረግ ጥረት እንደሚደረግ ለረቂቅ ኦዲት ሪፖርት በፅሁፍ በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

100. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ በመሆን ስራ ተቋራጮች በወሰዱት ፈቃድ መሰረት እየሰሩ መሆናቸውን ክትትል በማድረግ የፅሁፍ ግብረ-መልስ እንዲላክላቸው አለማድረጉ ስራ ተቋራጮች ያሉባቸውን ክፍተቶች/ችግሮች በወቅቱ በማወቅ ወደ ተሻለ አሰራር እንዳይሄዱ እና ችሮቻቸው ሊፈቱ የሚችሉባቸውን መንገዶች እንዳያውቁ ያደርጋቸዋል፡፡

**በፌዴራል ደረጃ ብቻ የሚሰጡ አገልግሎቶችን በተመለከተ፣**

101. በፌዴራል ደረጃ ብቻ የሚሰጡ አገልግሎቶች ተጠቃሚዎች በቀላሉ አገልግሎቱን የሚያገኙበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

102. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፌዴራል ደረጃ ብቻ የሚሰጡ አገልግሎቶች ተጠቃሚዎች በቀላሉ/በያሉበት ቦታ ወይም በቅርበት አገልግሎቱን እንዲያገኙ ለማድረግ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት ያልዘረጋ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

103. ስለ ሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ በፌዴራል ደረጃ ብቻ የሚሰጡ አገልግሎቶች በውክልና ለክልሎች ከመሰጠቱ በፊት አቅማቸው መታየት ያለበት በመሆኑ፣ የአሰራር ሥርዓት፣ አዋጆችና ደንቦች በመዘጋጀት ላይ በመሆናቸው፣ ከክልሎች ጋር በመመሪያዎች ዙሪያ ያሉ ክፍተቶች ላይ ቅድሚያ ውይይት ማድረግ የሚያስፈልግ በመሆኑ እንዲሁም ከኢትዮጵያ የመረጃ መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ጋር በመተባበር እየተሰራ ያለው የኦን-ላይን ምዝገባ እና የወረፋ አያያዝ ስራ ባለመጠናቀቁ እስካሁን አገልግሎቱን ክልሎች እንዲሰጡ ሊደረግ አለመቻሉን ገልፀዋል፡፡

104. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፌዴራል ብቻ የሚሰጡ አገልግሎቶች በክልሎችና ከተማ መስተዳድሮች ሁሉ እንዲሰጡ አለማድረጉ ተገልጋዮች ለጊዜ እና ገንዘብ ብክነት ይዳርጋቸዋል፡፡

**ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን ግንኙነት በተመለከተ፣**

105. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመገናኘት የምዝገባና የፈቃድ አሰጣጥ ሂደቱን ሊገመግም ይገባል፡፡

106. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከባለድርሻ አካላት በየሩብ በመገናኘት የምዝገባና የፈቃድ አሰጣጥ ሂደቱን መገምገም እንዳለበት በባለሙያዎችና ሥራ ተቋራጮች ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 19 ላይ የተጠቀሰ ቢሆንም ተግባራዊ አለማድረጉ ታውቋል፡፡

107. ስለ ሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በኦዲት ግኝቱ ላይ የተጠቀሱ ነገሮችን የሚቀበሉና በቀጣይነት በሚደረጉ የግምገማ መድረኮች የምዝገባ አሰራሩ እንደ አንድ አጀንዳ ተይዞ አፈፃፀሙ በጋራ የሚገመገምበት ሁኔታ የሚመቻች መሆኑን ለረቂቅ ኦዲት ሪፖርት በፅሁፍ በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

108. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሥራ ተቋራጮች ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ ሂደት ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በተመለከተ በየሩብ ዓመቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመገናኘት አለመገምገሙ በሂደቱ ላይ የሚታዩ ክፍተቶች ለይቶ በማውጣት በወቅቱ እርምጃ እንዳይወሰድባቸው ያደርጋል፡፡

## 2.2 የሥራ ተቋራጮችን የሚመለከቱ መረጃዎች አያያዝ እና አጠባበቅ እንዲሁም ቀልጣፋ የሆነ የመረጃ ልውውጥ ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፤

### ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን የመረጃ ልውውጥ በተመለከተ፣

109. ፈቃድ የወሰዱ ሥራ ተቋራጮችን በተመለከተ ከባለድርሻ አካላት (ትራስፖርት ሚ/ር፣ ከሠራተኛና ማህበራዊ ሚ/ር፣ የሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት…ወዘተ) ጋር የመረጃ ልውውጥ ማድረግ አለበት፡፡

110. ይህን እንጂ በ2008 ዓ.ም ፈቃድ የወሰዱ ሥራ ተቋራጮችን በተመለከተ ከባለድርሻ አካላት ጋር የሚያደርገውን የመረጃ ልውውጥ በተመለከተ ከትራንስፖርት ባለሥልጣንና ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን መስሪያ ቤት ጋር በመተባበር የመረጃ ልውወጡን በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ (Network) የታገዘ እንዲሆን ለማድረግ ታቅዶ ያልተከናወነ ሲሆን በ2009 በጀት አመት እቅድ ላይ ያልተያዘ መሆኑ ታውቋል፡፡

111. በተጨማሪም ከመንገድ ትራንስፖርት ጋር የተሽከርካሪዎችን መረጃ/ዳታ ቤዝ እንዲላክለት ከማድረግ፣ ከጉምሩክ ጋር የስራ ተቋራጮች ከውጭ ከቀረጥ ነፃ እንዲያስገቡ የድጋፍ ደብዳቤ እንዲፃፍላቸው ከማድረግ ውጭ ከቀረጥ ነጻ የገቡ ማሽነሪዎችን፣ መሳሪያዎችን እና ሌሎች ግባዕቶችን መረጃ በተመለከተ ከባለድርሻ አካላት ጋር የመረጃ ልውውጥ የማያደርግ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፤

112. ይህን በተመለከተ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ከመንገድ ትራንስፖርት ጋር የተሽከርካሪዎች ማስረጃዎችን ወቅታዊ /up-to-date/ በማድረግ፣ ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ጋር ስራ ተቋራጮች መሳሪያዎችን ከቀረጥ ነፃ እንዲያስገቡ ሲፈልጉ የትብብር ደብዳቤ በመፃፍ እና ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ መሳሪያዎችን መረጃ በመለዋወጥ ዙሪያ እንዲሁም ከየትምህርት ተቋማት የሚመረቁ ተማሪዎችን ዝርዝር መረጃ በመለዋወጥ ደረጃ ግንኙነት ያለው መሆኑን

እንደ አጠቃላይ ግን ከሁሉም ባለድርሻ አካላት ጋር መረጃዎችን በon-line መለዋወጥ ደረጃ ላይ አለመደረሱን ገልፀዋል፡፡

113. ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከመንገድ ትራንስፖርት ጋር የተሽከርካሪዎች ወቅታዊ ማስረጃዎች መለዋወጡን፣ ከገቢዎችና ጉምሩክ ጋር ከቀረጥ ነፃና ሌሎች ልውውጦች መደረጋቸውን የሚያሳዩ ማስረጃዎች ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ባለመቅረባቸው የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

114. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሥራ ተቋራጮችን በተመለከተ ከሁሉም ከባለድርሻ አካላት ጋር የመረጃ ልውውጦችን አለማድረጉ በሚሰጣቸው አገልግሎቶች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡

## ስለ ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የሚተነተኑ መረጃዎች ስርጭትን በተመለከተ፣

115. ስለ ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የተለያዩ መረጃ በመሰብሰብ ትንተና ሊያከናውን ይገባል፡፡ የሚተነተኑ መረጃዎችን በማሰባሰብ በተለያዩ ዘዴዎች (መፅሔት፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ብሮሽሮችን፣ ዌብ ሳይት …ወዘተ) በመጠቀም ሊያሰራጭ ይገባል፡፡

116. ይሁን እንጂ፡-

- በ2007 ዓ.ም በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ውስጥ የተሰማሩና የሚሰማሩ የተመዘኑ ባለሙያዎችን መረጃ በመሰብሰብ ዳታ ቤዝ ውስጥ ለማስገባት በእቅድ ቢያዝም ያልተከናወነ መሆኑ እና በ2008 እና በ2009 ዓ.ም እቅድ ያልተካተተ መሆኑ፣
- በ2008 ዓ.ም የዘርፉን አሰራር በኢንፎርሜሽን ኮሚኒዩኬሽን ቴክኖሎጂ የመደገፍ ተግባርን በተመለከተ የተቀናጀ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ የመረጃ ሥርዓት እንዲለማ ለማድረግ ታቅዶ ያልተከናወነና በ2009 በጀት ዓመት በእቅድ የተያዘ ቢሆንም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ያልተከናወነ መሆኑ፤
- በ2008 ዓ.ም ከሁሉ አማራጭ ምንጮች የተሰበሰበውን የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ባለሙያዎች መረጃ መተንተንን አቅዶ ያላከናወነና በ2009 በጀት አመት እቅድ ላይ የተያዘ ቢሆንም እስከ አንደኛው ሩብ ዓመት ድረስ አልተከናወነም፣

- በ2008 ዓ.ም ብቁ ሆነው የብቃት ማረገገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጣቸውን ባለሙያዎች መረጃ ከክልሎችና ከሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች በመሰብሰብ ዳታ ቤዝ ውስጥ ለማስገባት ታቅዶ ያልተከናወነ ሲሆን በ2009 ዓ.ም እቅድ ላይ ያልተካተተ መሆኑ፣
- በ2008 ዓ.ም የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን ነባራዊ ሁኔታ መረጃ ማሳባሰቢያ ቼክ ሊስት መጠይቅና ቢጋር ማዘጋጀትና የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን ነባራዊ ሁኔታ መረጃ ማሰባሰብ ታቅዶ ያልተከናወነ ሲሆን በ2009 ዓ.ም እቅድ ላይም ያልካተተ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

117. ስለ ሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በ2008 ዓ.ም ጥቅምት ወር የተቋቋመ እና በአደረጃጀት ላይ የነበረ በመሆኑ የተጠቀሱት ነገሮች ሊሰሩ አለመቻሉን ገልፀዋል፡፡

118. በኮንስትራክሽን ዘርፉ ላይ መረጃዎች እየተሰበሰቡ የማይተነተኑ ከሆነ የዘርፉ ችግሮችን በማወቅ መፍትሄ አቅጣጫ ማስቀመጥና የፖሊሲና የስትራቴጂ ሃሳብ ማመንጨት ላይ የራሱን አሉታዊ ተጽዕኖ ይኖረዋል፡፡

## ፈቃድ የወሰዱ ሥራ ተቋራጮችን የሚመለከቱ ማስረጃዎች በጥንቃቄ መያዛቸውን በተመለከተ፣

119. ፈቃድ የወሰዱ ሥራ ተቋራጮችን የሚመለከቱ ማስረጃዎች በጥንቃቄ ተይዘው ማህደር ውስጥ እንዲያዙና በሚፈለጉበት ጊዜ በቀላሉ እንዲገኙ በሚያስችል መልኩ ሊደራጁ ይገባል፡፡

120. ይሁን እንጂ ፈቃድ የወሰዱ የሥራ ተቋራጮች ማህደር በጥንቃቄ የማይያዙ እና የሚፈለጉ መረጃዎች በቀላሉ ሊገኙ በሚችሉበትና በቅደም ተከተል (chronological order) መልኩ የማይቀመጡ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩ ፋይሎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

121. ይህን በተመለከተ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በ2008 ዓ.ም መጨረሻ ላይ ከመከላከያ ሚኒስቴር በመጡ ባለሙያዎች እገዛ በፋይሉ ለሚገኙ እያንዳንዱ ቅጠል ቁጥር እንዲሰጣቸው በማድረግ ማህደሮች እንዳይጠፉ

ጥረት ተደርጎ የነበረ መሆኑን ነገር ግን በሰው ሃይል እጥረት እና በፋይሎች ለስራ ወጥቶ ቶሎ አለመመለስ ምክንያት ይህ ችግር ሊቀረፍ አለመቻሉን ገልፀዋል፡፡

122. የሥራ ተቋራጮችን ማኅደር በጥንቃቄ እና ቅደም ተከተሉን በጠበቀ መልኩ አለመያዙ ለሰነዶች መጥፋት እና ከዚህ ጋር ተያይዞ ሚኒስቴር መ/ቤቱን ለተጠያቂነት የሚዳርግ ከመሆኑም በተጨማሪ ተገልጋዮች እንዲንገላቱ ለማድረግ እና ለሙስና የሚያጋልጥ አሰራር ለመክፈት የራሱን አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡

## ክፍል ሶስት

### መደምደሚያ

123. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለሥራ ተቋራጮች ለሚሰጠው ፈቃድና ቁጥጥር ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የአሰራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ እያደረገ መሆኑ ሲገመገም የሚከተሉት ዋና ዋና ግድፈቶች ተገኝተዋል፡-

- የሥራ ተቋራጮችን ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ የሚመለከቱ አዋጆች፤ ለማስፈጸም የሚረዱ ደንቦች ያልወጡ መሆኑኑ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለመውሰድ እና በየዓመቱ ለማሳደስ የሚመጡ ስራ ተቋራጮች በሰነድ የሚያቀርቧቸው መሳሪያዎችና ተሽከርካሪዎች እና የሰው ኃይል በአካል ስለመኖራቸው የማይረጋገጥ መሆኑ፣ በተጨማሪም ሥራ ተቋራጮች በየፕሮጀክቶቻቸው የሚያሰሯቸው ሠራተኞች የብቃት ደረጃ ከሚሰሩት ተግባር ጋር ተመጣጣኝ መሆኑን የማያረጋግጥ መሆኑ፣
- ለሀገር በቀል የስራ ተቋራጮችን የሚደረገው ድጋፍ አነስተኛ መሆኑ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሥራ ተቋራጮች በየዓመቱ ፈቃዳቸውን ማደሳቸውን ክትትልና ቁጥጥር የማያደርግ እና ያላሳደሱትን ለይቶ በማውጣት ህብረተሰቡ፣ የግል ድርጅቶች፣ የመንግስት ተቋማት እና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት እንዲያውቁት የሚያደርግበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፣
- ሚ/ር መ/ቤቱ ፈቃድ የወሰዱ የሥራ ተቋራጮች ያስመዘገቧቸው (የሰው ኃይል፣ መሳሪያዎችና ተሽከርካሪዎች) ፈቃድ ለወሰዱበት ሥራ እየዋሉ መሆኑን የማያረጋግጥ መሆኑ፣
- የሥራ ተቋራጮች ፈቃድ ፈቃድ ለማውጣትና ለማሳደስ የሚያቀርቧቸው የመሳሪያዎች/ ተሽከርካሪዎች የባለቤትነት እና ሌሎች ተያያዥ ሁኔታዎች ዝርዝር የሚሳዩ መረጃዎች የሚመዘገብትና ወቅታዊ የሚያደርግበት ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከተሠጣቸው ደረጃ ውጭ የሚሰሩ የሥራ ተቋራጮች እንዳይኖሩ እና ፈቃዳቸውን ለሌላ አካል አሳልፈው የሚሰጡ የስራ

ተቋራጮች ለመከላከል የሚያስችል የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፣

- ለሥራ ተቋራጮች የሚሰጡ አገልግሎቶችን በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት አለመሆኑ እና ደንበኞች የሚጉላሉ መሆኑ፣
- ሚ/ር መ/ቤቱ የስራ ተቋራጮች ደረጃቸውን ለማሳደግም ሆነ ብቃታቸውን እንዲጨምር የሚያደርግ ሥልጠና ለመስጠት፣ ለመንግስትና ለህዝብ አገልግሎት የሚውሉ ግንባታዎች ከተጠናቀቁና የመጨረሻ ርክክብ ከተፈጸመ በኋላ የግንባታውን ሂደት ለማወቅ በ2008 እና 2009 ዓ.ም የክዋኔ ኦዲት ማንዋል ለማዘጋጀት እና ኦዲቱን ለማድረግ በአቅዱ ያላከናወነ መሆኑ፣
- በፌደራል እና በክልሎች የስራ ተቋራጮች ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ የተቀመጠው መስፈርት በተሌየ መንገድ የሚጠቀሙበት መሆኑ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልል የኮንስትራክሽን ዘርፍ ተቋማት እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት ስራ ተቋራጮች በተሰጣቸው የብቃት ማረጋገጫ መሰረት እየሰሩ መሆናቸውን ቁጥጥርና ክትትል የማያደርግ መሆኑ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፌዴራል ደረጃ ብቻ የሚሰጡ አገልግሎቶች ተጠቃሚዎች በቀላሉ/በያሉበት አገልግሎቱን ተደራሽ አለመሆኑ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመገናኘት የምዝገባና የፈቃድ አሰጣጥ ሂደቱን የማይገመግም መሆኑ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፈቃድ የወሰዱ ሥራ ተቋራጮችን በተመለከተ ከባለድርሻ አካላት ጋር የመረጃ ልውውጥ ያላደረገ መሆኑ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ስለ ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የሚተነተኑ መረጃዎችን የተለያዩ ዘዴዎች በመጠቀም የማያሰራጭ መሆኑ፣
- ሚ/ር መ/ቤቱ የስራ ተቋራጮችን ሰነድ በቀላሉ ሊገኝ በሚችል እና ቅደም ተከተሉን በጠበቀ መልኩ የማያሰቀምጥ መሆኑ፣

124. ስለሆነም በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን ድክመቶች እና ችግሮች ለማስወገድ ወይንም ለማቃለል አስተዋፅኦ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል አቅርበናል፡፡

## ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሃሳቦች

125. ለሥራ ተቋራጮች ለሚሰጠው ፈቃድና ቁጥጥር ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የአሰራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ለማድረግ ያስችላሉ ያልናቸውን የሚከተሉት የማሻሻያ ሃሳቦች አቅርበናል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የምዝገባና የፈቃድ አሰጣጥ ሂደቱን ሥራ ላይ ለመዋል ለወጡ አዋጆች ማፈጸሚያ የሚሆኑ ደንቦች በፍጥነት ተዘጋጅተውና በሚመለከተው አካል ሊጸድቁ ይገባል፡፡ ደንቦቹንም ለማፈጸም ሚረዱ መመሪዎያዎችም በተጓዳኝ ሊዘጋጁና ተግባራዊ ሊደረጉ፣ ከዚህ በፊት የወጡ መመሪያዎችም ከደንቡ ጋር የተጣጣሙ መሆናቸው ሊረጋገጥ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሁሉም ዓይነት የስራ ተቋራጭነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለመውሰድ እና በየዓመቱ ፈቃዳቸውን ለማሳደስ የሚመጡ ሥራ ተቋራጮች በሰነድ የሚያቀርቧቸው መሳሪያዎች፣ ተሽከርካሪዎችና የሰው ኃይል በአካል መኖራቸውን የሚያረጋግጥበት የአሰራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ በተጨማሪም እነዚሁ የሥራ ተቋራጮቹ የሚወስዷቸው የኮንትራክት ፕሮጀክቶች ተገቢውን የሙያ ብቃት ደረጃ ያሟሉ የሰው ኃይል በየፕሮጀክቱ ማሰማራታቸውን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት የሚረጋገጥበት አሰራር ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደረግ ይገባል፡፡
- ሚኒስትር መ/ቤቱ የሀገር በቀል የሥራ ተቋራጮች በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ውጤታማ እንዲሆኑ እና አለም አቀፍ ተወዳዳሪ ለማድረግ የሚያስችሉ የድጋፍ ዓይነቶችን ለይቶ በማጥናት ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአገር ውስጥ የስራ ተቋራጮች ያሉባቸውን ክፍተቶች በማወቅ እና መሠጠት ያለባቸውን የስልጠና ዓይነቶች ለይቶ በማውጣት ወቅቱን የጠበቁ ሥልጠናዎችን የሚያገኙበትን ሁኔታ በማመቻቸት

ለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ከፍተኛ ሚና እንዲጫወቱ ማድረግ አለበት፡፡

- ሚ/ር መ/ቤቱ ፈቃድ የወሰዱ ሥራ ተቋራጮች በየዓመቱ የእድሳት ጊዜያቸውን ጠብቀው ያላሰደሱ የሥራ ተቋራጮች ሥራ ላይ እንዳይሰማሩ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግና ፈቃዳቸውን ያደሱ ~~ያላሳደሱ~~ ሥራ ተቋራጮችን ዝርዝር የተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች (ቴሌቪዥን፣ ሬዲዮ፣ ጋዜጣ፣ ዌብሳይት .... ወዘተ) በመጠቀም ህብረተሰቡ፣ የግል ድርጅቶች፣ የመንግስት ተቋማት እና የሚመለከታቸው አካላት እንዲያውቁት፣ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፈቃድ የወሰዱ ሰራ ተቋራጮች የብቃት ማረጋገጫውን ለማግኘት ያስመዘገቧቸውን (የሰው ኃይል፣ መሳሪያዎችና ተሽከርካሪዎች) ለተባለለት ዓላማ/ሥራ እየዋሉ መሆናቸውን በየዓመቱ በእቅድ ይዞ በማረጋገጥ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድባቸው የሚያስችለውን ሁኔታ ሊያመቻች ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመሳሪያዎች/ተሽከርካሪዎች ዝርዝር መረጃ የባለቤትነት እና ሌሎች ተያያዥ ሁኔታዎች የሚሳዩ መረጃዎችን በመመዝገብና ወቅታዊ በማድረግ በአንድ መሳሪያ ብዛት ያላቸው የሥራ ተቋራጮች ፈቃድ እንዳያወጡ ለማድረግ እነዲሁም የመሳሪዎችን ዝውውር ለመከታታል የሚያስችል አሰራር መዘርጋት ይጠበቅበታል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከተሠጣቸው ደረጃ ውጭ የሚሰሩ የሥራ ተቋራጮች እንዳይኖሩ፣ እንዲሁም ፈቃዳቸውን ለሌላ አካል አሳልፈው የሚሰጡ የስራ ተቋራጮች በቅድሚያ ለመከላከል የሚያስችል ሲገኙም እርምጃ የሚወሰድበት የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ በማድረግ በሕገ-ወጥ የብቃት ማረጋገጫ የሚሰሩ ስራ ተቋራጮችን መከላከል አለበት፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለሥራ ተቋራጮች የሚሰጣቸው የፈቃድና የምዝገባ አገልግሎቶች በተቀመጠው የአገልግሎት መስጫ የጊዜ ገደብ መሰረት እንዲስተናገዱ በማድረግ እና በየጊዜው ከተገልጋዮች የሚነሱ ቅሬታዎችና ፍላጎቶችን በመለየት የታዩ ክፍተቶችን እየገመገመ ማስተካከል


የሚችልበት ስርአት ዘርግቶ ተግባራዊ በማድረግ ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት መስጠት አለበት፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለመንግስትና ለህዝብ አገልግሎት የሚውሉ ግንባታዎች ከተጠናቀቁና የመጨረሻ ርክክብ ከተፈጸመ በኋላ የግንባታውን ሂደት በማወቅ የታዩ ግድፈቶች እንዲታረሙ እና በቀጣይ ለሚከናወኑ ግንባታዎች ግብአት መሆን እንዲችል መታየት ያለባቸው የግንባታ ፕሮጀክቶችን ከየዘርፉ በዕቅድ ይዞ ያላከናወናቸውን የማናዋል ዝግጅት በማጠናቀቅ እና በእቅድ በመያዝ የክዋኔ ኦዲት ማከናወን አለበት፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፌዴራል ደረጃ የሚከናወነው የስራ ተቋራጮች ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ በወጣው ስታንደርድ መሰረት ከክልሎች ጋር ወጥ እንዲሆን ከሚመለከታቸው የክልል አካላት ጋር በቅንጅት መስራትእና ተገቢውን ድጋፍ መስጠት ይተቅበታል፡፡
- ሚ/ር መ/ቤቱ ከክልል የኮንስትራክሽን ዘርፍ ተቋማት እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት ስራ ተቋራጮች በተሰጣቸው የብቃት ማረጋገጫ መሰረት እየሰሩ መሆናቸውን ቁጥጥርና ክትትል ሊያደርግና በክትትሉ ወቅት የተገኙ ክፍተቶችን ለማረም/ለማስተካከል እንዲችሉ የፅሁፍ ግብረ መልስ ሊሰጥ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፌዴራል ደረጃ ብቻ የሚሰጡ አገልግሎቶች ተጠቃሚዎች በቀላሉ አገልግሎቱን በያሉበት እንዲያገኙ የሚያስችላቸውን የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ በማድረግ ቀልጣፋ አገልግሎት ከክልሎች ጋር በመቀናጀት ወይም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በመክፈት ካለሆነም ሌላ አማራጭ በማጥናት ተግባራዊ በማድረግ ተገልጋዮች ለአላስፈላጊ ለሆነ የገንዘብና ወጪ እና የጊዜ ብክነት እንዳይጋለጡ ማድረግ አለበት፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመመሪያው ላይ ባስቀመጠው መሰረት በየሩብ ዓመቱ በመገናኘት የምዝገባና የፈቃድ አሰጣጥ ሂደቱን ላይ ያጋጠሙ ችግሮችን በተመለከተ በጋራ በመገምገም የመፍትሄ እርምጃ ሊሰጥ ይገባል፡፡ ይህ የማያሰራው ከሆነም በመከለስና ከሚመለከታቸው ጋር በመመካከር የምክክር መድረኩን ሊያካሂድ ይገባል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፈቃድ የወሰዱ ሥራ ተቋራጮችን በተመለከተ ከባለድርሻ አካላት Net-worked የሆነ የመረጃ ልውውጥ ስርዓት ዘርግቶ ሊጠቀም ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ስለ ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የሚተነተኑ መረጃዎችን ወቅታዊ በማድረግ እና በማሰባሰብ በተለያዩ ዘዴዎች (መፅሔት፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ብሮሽሮችን፣ ዌብ ሳይት ...ወዘተ) በመጠቀም በማሰራጨት መረጃዎቹ ለተጠቃሚዎች ተደራሽ እንዲሆኑ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- የስራ ተቋራጮችን የሚመለከቱ ማንኛውም ሰነዶች ዘመናዊ በሆነ የመረጃ አያያዝ ዘዴ በመጠቀም ሊያደራጃቸው እና ጥንቃቄ ሊደረግላቸው እና በተገልጋዮች ሲፈለጉ በቀላሉ ሊገኙ እንዲችሉ ቅደም ተከተላቸውን በጠበቀ መልኩ እንዲቀመጡ በማድረግ አገልግሎት አሰጣጡን የተቀላጠፈ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

126. በመጨረሻም ለኮንስትራክሽን ሚኒስቴር፣ በኦዲት ወቅት ለታዩት ለአዲስ አበባ ኮንስትራክሽን ቢሮ፣ ለኦሮሚያ ኮንስትራክሽን ቢሮ፣ በናሙና ተመርጠው ለታዩ ሥራ ተቋራጮች የሥራ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች በኦዲቱ ወቅት ስላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

# አባሪ 1፡ የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ድርጅታዊ መዋቅር



# አባሪ 2፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria)

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች /Audit Issues/ | የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች /Evaluative Criteria/ |
|---|---|
| 1.ሚ/ር መ/ቤቱ ለስራ ተቋራጮች የሚሰጠው የብቃት ማረጋገጫ፣ ምዝገባና ቁጥጥርን በተመለከተ የወጡ ደንቦችና መመሪያዎችን ማስፈፀም የሚያስችል ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ የአሠራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፣<br><br>1.1. ሚ/ር መ/ቤቱ የስራ ተቋራጮችን ብቃት በማረጋገጥ የሚመዘግብበት እና በየበጀት ዓመቱ ቁጥጥር የሚያደርግበት ስርዓት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፣ | 1. በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ዘርፍ ለሚሰማሩ የሥራ ተቋራጮች ፈቃድ አሰጣጥን የሚመለከቱ አዋጆችን ለማስፈፀም የሚረዱ ደንቦችና መመሪያዎች ተዘጋጅተው በሚመለከተው አካል ጸድቀው ተግባራዊ ሊደረጉ ይገባል፡፡ |
| | 2. ለሁሉም አይነት ሥራ ተቋራጮች (ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ፣ የህንፃ ሥራ ተቋራጭ፣ የመንገድ ሥራ ተቋራጭ እና ልዩ ሥራ ተቋራጭ) የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሲሰጥ በየደረጃው የተቀመጠውን መስፈርት (የመሳሪያ፣ የካፒታል መጠንና የሰው ኃይል) ያሟሉ መሆኑ የሚያረጋግጥበት የአሠራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 3. በሁሉም አይነት ሥራ ተቋራጭነት (ጠቅላላ፣ የህንፃ ፣ የመንገድ እና ልዩ ሥራ ተቋራጭ) መሳተፍ ለሚፈልጉ የውጭ አገር ሥራ ተቋራጮች የሚሰጠው ፈቃድ ደረጃ አንድ ብቻ ሊሆን ይገባል፡፡ |
| | 4. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለሥራ ተቋራጮች ፈቃድ አሰጣጥ ሂደት ግብዓት ሊሆኑ የሚችሉ እና ችግር ፈቺ የሆኑ ጥናቶች ተጠንተው ተግባራዊ እንዲሆኑ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 5. ሚኒስትር መ/ቤቱ የሀገር በቀል የስራ ተቋራጮች በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ውጤታማ እንዲሆኑ ሊደግፍ ይገባል፡፡ |
| | 6. የሥራ ተቋራጮች በየፕሮጀክቶቻቸው የሚያሰማሯቸው ሠራተኞች የብቃት ደረጃ ከሚያሠሯቸው ተግባር ጋር ተመጣጣኝ መሆኑን ሚ/ር መ/ቤቱ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ |
| | 7. ለአገር ውስጥ የስራ ተቋራጮች የተለያዩ ሥልጠናዎችን |

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች /Audit Issues/ | የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች /Evaluative Criteria/ |
|---|---|
| | በመስጠት ደረጃቸውን እንዲያሳድጉ በማመቻቸት ብቃታቸው እንዲጨምር የሚያደርግበት የአሠራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 8. ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ፈቃድ የወሰዱ ሥራ ተቋራጮች በየዓመቱ ፈቃድ ያሳደሱ መሆናቸውን መከታተልና መቆጣጠር አለበት፡፡ |
| | 9. የሥራ ተቋራጮች ፈቃድ ሲታደስ ለደረጃቸው የሚያስፈልገው (የሰው ኃይል፣ መሳሪያዎችና ተሽከርካሪዎች) በሠነድና በአካል መኖራቸው የሚረጋገጥበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 10. ፈቃድ የወሰዱ የሥራ ተቋራጮች ያስመዘገቧቸው (የሰው ኃይል፣ መሳሪያዎችና ተሽከርካሪዎች) ፈቃድ ለወሰዱበት ሥራ እየዋሉ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል (በስራ ቦታው ላይ ድንገተኛ ጉብኝት በማድረግ የተመዘገቡት መሳሪያዎች በስራ ላይ ስለመሆናቸው) በየአመቱ እቅድ በማዘጋጀት የሚጣራበት የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 11. በአንድ መሳሪያ ብዛት ያላቸው የሥራ ተቋራጮች ፈቃድ እንዳያወጡ ለማድረግ የመሳሪያዎች ዝርዝር መረጃ የባለቤትነት እና ሌሎች ተያያዥ ሁኔታዎች የሚሳዩ መረጃዎች የሚመዘገብትና ወቅታዊ የሚደረጉበት ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 12. ፈቃድ ያላሳደሱ ሥራ ተቋራጮች በተቋራጭነት ስራ ላይ እንዳይሰማሩ ለማድረግ ህብረተሰቡ፣ የግል ድርጅቶች፣ የመንግስት ተቋማት እና የሚመለከታቸው አካላት |

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች /Audit Issues/ | የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች /Evaluative Criteria/ |
|---|---|
| | እንዲያውቁት የሚደረግበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡ |
| | 13. ከተሠጣቸው ደረጃ ውጭ በሚሰሩ የሥራ ተቋራጮች እንዳይኖሩ ለመከላከል ሚያስችል የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 14. ፈቃዳቸውን ለሌላ አካል አሳልፈው የሚሰጡ የስራ ተቋራጮች የሚጠየቁበት የአሰራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 15. ለሥራ ተቋራጮች የሚሰጡ አገልግሎቶች በተቀመጠው የአገልግሎት መስጫ የጊዜ ገደብ (አዲስ ምዝገባ 1:45 ሰዓት፣ እድሳት 1:32 ሰዓት፣ የደረጃ/የዘርፍ ለውጥ 1:32 ሰዓት የጠፉ ብቃት ማረጋገጫ ምትክ ጥያቄ 0.65 ሰዓት፣ ፈቃድ ስረዛ ፈቃድ የወሰደው አካል ሲመለስ 0.28 ሰዓት እና በቅጣት ሲሰረዝ 0.41 ሰዓት) መሰረት ሊከናወኑ ይገባል፡፡ |
| | 16. ለመንግስትና ለህዝብ አገልግሎት የሚውሉ ግንባታዎች ከተጠናቀቁና የመጨረሻ ርክክብ ከተፈጸመ በኋላ የግንባታውን ሂደት ለማወቅ የክዋኔ ኦዲት የሚከናወነበት የአሰራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 17. በፌደራል እና በክልሎች ያለው በየደረጃው የሚከናወነው የስራ ተቋራጮች ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ ተመሳሳይ ስታንዳርድ እንዲኖረው ለማድረግ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት እንዲዘረጋ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ሊሰራ ይገባል፡፡ |
| | 18. ሚኒስትር መ/ቤቱ የመንግስት ግንባታዎች በታቀደላቸው ጊዜ፣ ወጪ እና የጥራት ደረጃ እንዲጠናቀቁ በአመታዊ ዕቅድ በመያዝ ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡ |

| **የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች** /Audit Issues/ | **የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች** /Evaluative Criteria/ |
|---|---|
| | 19. ሚኒስትር መ/ቤቱ የመንግስት ግንባታዎችን በታቀደላቸው ጊዜ፣ ወጪ እና የጥራት ደረጃ ያላጠናቀቁ የስራ ተቋራጮች የሚቀጡበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 20. ሚኒስትር መ/ቤቱ የተገልጋዮችን ፍላጎት እርካታን ለማወቅና ክፍተቶቹን እየገመገመ ለማስተካከል የሚያስችል ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረግ በየጊዜው ማስተካከል አለበት፡፡ |
| 1.2 **ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው የመንግስት መ/ቤቶች እና ባለድርሻ አካላት ጋር የሥራ ተቋራጮችን ውጤታማ ለማድረግ እና ለመደገፍ በቅንጅት የሚሰሩበት አሰራር መዘርጋቱንና ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፣** | 21. ሚ/ር መ/ቤቱ ከክልል የኮንስትራክሽን ዘርፍ ተቋማት እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት (የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ መንገድ ትራንስፖርት፣ የሙያ ማህበራት፣ ኢንሹራንስ….ወዘተ) ጋር በመቀናጀት መከታተል የሚያስችል ቼክ ሊስትና የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ስራ ተቋራጮች በተሰጣቸው የብቃት ማረጋገጫ እየሰሩ መሆናቸውን ቁጥጥርና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 22. ከባለድርሻ አካላት ጋር በተደረገው ቁጥጥርና ክትትል መሰረት ለሥራ ተቋራጮች የፅሁፍ ግብረ መልስ ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| | 23. በፌዴራል ደረጃ ብቻ የሚሰጡ አገልግሎቶች ተጠቃሚዎች በቀላሉ አገልግሎቱን የሚያገኙበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 24. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር በየሩብ ዓመቱ በመገናኘት የምዝገባና የፈቃድ አሰጣጥ ሂደቱን ሊገመግም ይገባል፡፡ |
| | 25. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሙያ ማህበራት (የስራ ተቋራጮች፣ አርክቴክቶች ቀያሾች፣ መሐንዲሶች ወዘተ) የላቀ ተሞክሮ |

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች /Audit Issues/ | የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች /Evaluative Criteria/ |
| --- | --- |
| | ካላቸው የውጭ የሙያ ማህበራት የክህሎት ሽግግር የሚያደርጉባቸውን መድረኮች ማመቻቸት አለበት፡ |
| 2. የሥራ ተቋራጮችን የሚመለከቱ መረጃዎች አያያዝ እና አጠባበቅ እንዲሁም ቀልጣፋ የሆነ የመረጃ ልውውጥሥርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፣ | 26. 26. ፈቃድ የወሰዱ ሥራ ተቋራጮችን በተመለከተ ከባለድርሻ አካላት (ትራስፖርት ሚ/ር፣ ከሠራተኛና ማህበራዊ ሚ/ር፣ የሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት…ወዘተ) ጋር የመረጃ ልውውጥ ማድረግ አለበት፡፡ |
| | 27. ስለ ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የሚተነተኑ መረጃዎችን በማሰባሰብ በተለያዩ ዘዴዎች (መፅሔት፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ብሮሽሮችን፣ ዌብ ሳይት …ወዘተ) በመጠቀም ሊያሰራጭ ይገባል፡፡ |
| | 28. ፈቃድ የወሰዱ ስራ ተቋራጮችን የሚመለከቱ ማስረጃዎች በጥንቃቄ ተይዘው ማህደር ውስጥ እንዲያዙና በሚፈለጉበት ጊዜ በቀላሉ እንዲገኙ መደረግ አለበት፡፡ |

## አባሪ 3፡ በኦዲቱ ወቅት በናሙና የታዩ ቢሮዎች፣ ሥራ ተቋራጮች እና ባለድርሻ አካላት እና ዝርዝር

| ተራ ቁጥር | ቢሮዎች | ሥራ ተቋራጮች | ባለድርሻ አካላት |
|---|---|---|---|
| 1. | • የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኮንስትራክሽን ቢሮ፣<br>• የኦሮሚያ ክልል ኮንስትራክሽን ቢሮ፣ | - ሰንሻይን<br>- ማክሮ<br>- ሮኬት<br>- ሚካዳ<br>- ዳታ<br>- ጉተማ ፉሪሳ<br>- አንዋር ሰይድ<br>- እሸቱ ለማ<br>- ፖወር ኮን እና<br>- ድሪባ ደፈርሻ | የሰነዶች ማረጋገጫ ኤጀንሲ |